# የግብረ-ገብ ትምህርት

# የመምህራን መምሪያ

# 3ኛ ክፍል

**ተርጓሚዎች፡-**

**አበራ ከበበው**

**ገብረሚካኤል አቦምሳ**

**ይልፋሸዋ ጥላሁን**

**አርታኢዎች-**

በላይነሽ ደነቀ (ዶክተር)

በርናባስ ደበሎ

አበባየሁ ደምሴ

**ገምጋሚ**

**ደረጀ መኮንን**

**ግራፍክስ**

**ታደሰ ድንቁ**

**ሠዓሊ፡** ብዙአየሁ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ መጽሀፍ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርና መነሻነት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስተባባሪነት ተስማምቶና ተተርጉሞ ተዘጋጀ፡፡ ስለዚህ በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# ማዉጫ

**ምዕራፍ 1: ሰብዓዊ ክብር ........ 1**

1.1: ሰብአዊነት(የተሰጠ የክፍል ጊዜ ብዛት 5) ........ 2

ትምህርት 1.2: የሰው ልጅ ክብር ........ 6

ትምህርት 1.3: መሠረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ........ 11

**ምዕራፍ 2: ሰዎችን ማክበር ........ 23**

2.1: ሰዎችን ማክበር ........ 23

2.2: ሰዎችን የማክበር አስፈላጊነት ........ 27

2.3: የተከበሩ ሰዎች የሚታወቁባቸው ባህሪያት ........ 31

2.4: ሰዎችን ካለማክበር የሚከሰቱ ችግሮች ........ 34

**ምዕራፍ ሦስት፡ እኩልነት ........ 42**

3.1. የእኩልነት ምንነት ........ 42

3.2. እኩልነት በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ ........ 46

3. 3. የእኩልነት አስፈላጊነት ........ 50

**ምዕራፍ አራት፡ ማሕበራዊ ሕይወት ........ 57**

ትምህርት 4.1 የማህበራዊ ሕይወት ምንነት ........ 57

4.2 መልካም ማህበራዊ ሕይወት ያለው ሰው ባህሪይ ........ 61

ትምህርት 4.4 የማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮች ........ 64

**ምዕራፍ 5፡መተጋገዝ እና አብሮ መስራት ........ 69**

ምዕራፍ 5፡1 መተጋገዝ እና አብሮ መስራት ........ 69

5.2፡በማህበረሰብ እና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትብብር እና የቡድን ስራ ባህል ........ 72

5.3፡መተጋገዝ እና አብሮ የመስራት መርሆዎች፤ ........ 75

5.4፡መተጋገዝ እና አብሮ የመስራት ባህል፤ .................................................... 77

ምዕራፍ 6፡ባህል ........................................................................................ 82

6.1፡መድብለ ባህላዊነት .............................................................................. 83

6.2፡የባህል ብዝሀነት መሰረቶች ......................................................................... 86

6.3፡የባህል ብዝሀነትን ማስተናገድ አስፈላጊነት ............................................... 89

6.4፡መድብለ ባህላዊነትን ማስተናገድ የሚቻልባቸው መንገዶች .................. 92

**3ኛ ክፍል ሲለበስ .......................................................................................... 99**

# ምዕራፍ 1: ሰብዓዊ ክብር

**የተሰጠ የክፍል ጊዜ ብዛት: 18 ክፍል ጊዜ**

## መግቢያ

**መምህር፤** ይህ ምዕራፍ ተማሪዎችን የሰብአዊነትን ምንነት እና የሰው ልጅ ክብርን ያስገነዝባል፡፡ የሰው ልጅን የማክበር አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤ የሚሰጥ እና መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን (እንደ ፍቅር፣ ርህሩህነት፣ደግነት፣ በጎ አድራጊት፣ ሰውን ማክበር፣ ትዕግስተኛ መሆን፣ ወንድማማችነት እና ሰላም መግለፅ እንዲችሉ ማድረግና በመጨረሻም የሰው ልጅን አለማክበር እና ሰብአዊ ባህሪያትን አለማንፀባረቅ ምን እንደሆኑ መዘርዘር እንዲችሉ ያደርጋል፡፡

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:**

- የሰብአዊነትን ትርጉም ይገልፃሉ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፤
- የሰብአዊ ክብርን አስፈላጊነት ይለያሉ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን በተግባር ያሳያሉ፤
- በሰዎች አለመከባበር ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ይለያሉ፡፡

## 1.1: ሰብአዊነት

*(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 5)*

**ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤**

- ሰብአዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ መሆኑን ይለያሉ፡፡

2. ይዘት፡
   - ሰብአዊነት
   - የሰው ልጆች ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ የሆኑባቸውን ባህሪያት መለየት

### 3. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

መምህር፡- በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ስለሰብአዊነት ይማራሉ፡፡ የሰብአዊነት መገለጫዎች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም ሰው መሆን እና የሰው ልጅ መገለጫ ባህሪያትን መያዝ ናቸው፡፡ ሰብአዊነት የሚለው ቃል አጠቃላይ የሰው ዘርን የሚገልፅ ነው፡፡ ሰብአዊነት የሚለው ቃል የመጣው የሰው ዘር ከሚለው ሲሆን ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን የተለየ ፍጥረት ስለሆነ የተለየ ፍቅር እና ክብር ይገባዋል፡፡ የሰው ልጅ በዘር፣ በፆታ፣ በቁመት፣ በቋንቋ እና በመሳሰሉት ልዩነት ቢኖረውም በሰብአዊነቱ ግን አንድ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች መሰረት በማድረግ ሰብዓዊ መብቱ ሊገፈፍ አይገባም፡፡

የሰብአዊነት መገለጫዎችን መሰረት በማድረግ ሲታይ ሰዎች አብሮ ለመኖር ሊያከብሯቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ መረዳት የሚገባቸውን ሰዎች ያለምንም ተፅዕኖ እና አድልዎ መርዳት፤ መተጋገዝ እና በሰዎች መካከል የመተባበር መንፈስ እንዲዳብር ማድረግ፤ የመረዳዳት ባህል እና ሰላማዊ ኑሮ በሰዎች እና በተማሪዎች መካከል እንዲፈጠር ማድረግ፤ የመረዳጃ ተቋማትን ማቋቋም፤ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እና ውጪ በችግር ጊዜ የመደጋገፍ እና የመረዳዳት ባህል እንዲያዳብሩ ማድረግ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 4. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች:

- ስዕል1.1. የሚያሳየው በሰዎች መሃከል ልዩነቶች ቢኖሩም በሰብአዊነታቸው ግን አንድ መሆናቸውን ነው፡፡
- በክፍል ውስጥ ያሉ ሁኔታዎችን በክፍሉ ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር በመሆን መገምገም፡፡

### መማር እና ማስተማር

የግንዛቤ ጥያቄ

- ተማሪዎች ሁለት ሁለት በመሆን ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማድረግ፤
- አጭር ገለፃ፤
- የቡድን ሥራ፤

## 6. የመማር ማስተማር ሂደት

ለትምህርት የሚደረጉ ዝግጅቶች

- የሰብአዊነት ፅንሰሃሳብ ላይ የተለያዩ መፃህፍትን ማንበብ፤
- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የሚገኙ ስዕሎችን መረዳት፤
- የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት

## 7. ትምህርቱን ማቅረብ

### ሀ. መግቢያ

- ሰብአዊነት የሚለውን የትምህርት ርዕስ ለተማሪዎች ማስተዋወቅ፤
- የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች መግለፅ፤
- የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ ለምሳሌ፡ በአከባቢያችሁ ያሉ ሰው ያልሆኑ ፍጡራን ምን ምንድን ናቸው?
- የትምህርቱን ርዕስ “ሰብአዊነት ምንድን ነው?” የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ ማስጨበጥ፤

### ለ. አቀራረብ

- የሰብአዊነትን ምንነት መግለፅ፤
- የሰብአዊነት መገለጫዎችን መዘርዘር፤
- ሁለቱን የሰብአዊነት መገለጫዎች መግለፅ፤
- በስዕል 1.1 ያለውን ተማሪዎች እንዲመለከቱ በማድረግ ከሰብአዊነት ጋር ያለውን ግንኙነት መግለፅ፤

### ሐ.ማጠናከሪያ

- ተማሪዎች ሰብአዊነት ምን እንደሆነ እንዲገልፁ መጠየቅ፤
- ሰብአዊነት የሚገለፅባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች ተማሪዎች እንዲያስታውሱ ማድረግ፡

- ተማሪዎች የሰው ልጅን ከሌሎች ነገሮች በመለየት ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤

## መ. ክትትል እና ግምገማ

- ሰብአዊነት በሚለው ላይ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ መጠየቅ፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በተግባር 1 ሥር የቀረበውን ጥያቄ እንዲሰሩ ማመቻቸት፡፡
  - በተማሪዎች በሚነሱና ከሰው ልጅ ባህርያት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦችን እንዲለማመዱ መርዳት፡፡
  - ይህንን ባህሪይ እንዴት እንደሚተገብሩ ያላቸውን ልምድ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ማድረግ፡፡
  -

# ትምህርት 1.2: የሰው ልጅ ክብር

(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛትi 5)

## 1.ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች፤

የሰው ልጅን ክብር ምንነት ትገልፃለህ፡፡

## 2. ይዘት

- የሰው ልጅ ክብር ምንነት

## 3. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

መምህር፡- በዚህ የትምህርት ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ስለ ሰው ልጅ ክብር እና የመከባበር አስፈላጊነት ይማራሉ፡፡ የሰው ልጅ ክብርን በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ጉዳይ የሰው ልጅ ክብር ቋሚ እና በቅብብሎሽ የሚቀጥል ሲሆን ሰው የሰው ዘር በመሆኑ ብቻ የሚገባውን ክብር ማግኘቱን የሚገልፅ ነው፡፡ የሰው ልጅን ልዩ ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ ሚዛናዊ የሆነ አስተሳሰብ መኖር፤ ራስን ችሎ ውሳኔዎችን መስጠት መቻል፤ ሰብአዊ ምግባሮችን በነፃነት መለማመድ መቻል እና ለሌሎች ሰዎች ክብር የሚሰጥበት እሴት ያለው መሆኑ ነው፡፡ የሰው ልጅ ልዩ ፍጡር እና ከሌሎች ፍጡራን የተለየ ነው፡፡ ከሌሎች ፍጥረታትም በላይ ክብር እና ፍቅር ይገባዋል፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ የሰው ልጅ ክብር በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚለዋወጥ መሆኑና ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ የሚገኝ

ወይም የሚጠፋ መሆኑ ነው። ሰዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ ባላቸው ባህሪያት መሰረት ባህሪያቸው ጥሩ ከሆነ የሚከበሩ፤ ጥሩ የሆነ ባህሪይ ከሌላቸው ደግሞ የማይከበሩ መሆናቸው ነው።

**መከበር፡-** ሰው ለራሱ መስጠት የሚገባውን ቦታ ከሰጠ ክብርን ማግኘት ይችላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ለራሱ የሚገባውን ቦታ ወይም ዋጋ አለኝ ብሎ ራሱን ካሳመነ የሚገባው ክብር ይኖረዋል። በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ባህሪይ እና እሴት መሰረት የሚያደርግ ከሆነ ክብር ማግኘት ይችላል። ይህ ማለት ሰዎች በማህበረሰቡ እሴት መሰረት ባህሪያቸውን የሚያንፀባርቁ ከሆነ ጥሩ ሥነ-ምግባር ይኖራቸዋል።

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ለሌሎች ሰዎችም አርዓያ ይሆናሉ። ለምሳሌ፡- ወ/ሮ አበበች ጎበና ለማህበረሰቡ ባደረጉት በጎ ተግባር የተነሳ ትልቅ ክብር አላቸው። ይህ በማህበረሰቡ እሴት ውስጥ በጣም ተወዳጅ እና ትልቅ ክብር ያላቸው እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

**ክብር ማጣት፡-** ሰዎች ለራሳቸው ዋጋ የማይሰጡ ከሆነ ክብርን ያጣሉ። ክብር ከሚያሳጡ ነገሮች ውስጥ አንዱ ራስ ወዳድነት ነው። ለሰው ልጅ የሚገባውን ክብር ከሚያሳጡ ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹ መስረቅ፣ መዋሸት፣ አለመታመን እና የመሳሰሉት ናቸው። ሰው ክብር ማግኘቱ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። ሰው ሌሎችን ሰዎች የሚያከብር ከሆነ ለራሱ ክብር ያገኛል።

የሰው ልጅን ሰው በመሆኑ ብቻ ማክበር መሰረታዊ ሰብአዊ መብት ነው፡፡ የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቶች መገፈፍ የለባቸውም፡፡ በተጨማሪም የሰው ልጅ ክብር ለሰብአዊ እርዳታ እንደመሰረት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ጓደኛህ/ሽ ከአንተ/ች እርዳታ የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነ መርዳት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ውሃ፣ ምግብ፣ ልብስ እና የመሳሰሉትን ሲፈልጉ እርዳታ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕል (2) አርዓያ ሆነው የሚያገለግሉ እንደ አበበች ጎበና ያሉ ሰዎች ሥዕሎች
- ለሰዎች እርዳታ በመስጠት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታወቁ ሰዎች ሥዕል በመርጃ መሳሪያነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 5. የመማር ማስተማር ዘዴ

መምህራን፡- ተማሪዎች በሦስት ጎን ቅርፅ ቡድን በመስራት
የሰው ልጅ ክብር
እና አስፈላጊነት ላይ ውይይት እንዲያደርጉ አድርጉ፡፡

- የገለፃ ዘዴን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን ማቀናጀት

## 6. የመማር ማስተማር ሂደት

ለትምህርቱ የሚደረጉ ዝግጅቶች

- የሰው ልጅ ክብር እና የክብር አስፈላጊነት ላይ መፃህፍትን ማንበብ፤¡

- የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት፤

## 7. የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

- የሰውን ልጅ ክብር  እና የክብርን አስፈላጊነት ለተማሪዎች ማስተዋወቅ፤
- የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ማሳወቅ፤
- የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ፤ “ክብር ማለት ምን ማለት እንደሆነ መናገር ትችላለህ/ሽ?”
- “የሰው ልጅን ማክበር ምን ጠቀሜታ እንዳለው መግለፅ ትችላለህ/ሽ?”
- የትምህርቱን ይዘት መጠየቅ፤ የሰው ልጅ ክብር ምንድን ነው፤?” አስፈላጊነቱስ ምንድን ነው?”

### ለ. አቀራረብ

- የሰውን ልጅ ክብር አስፈላጊነት እና ምንነት መግለፅ፤
- የሰውን ልጅ ክብር ለመገንዘብ የሚያስችሉ ሁለት ነገሮችን በመግለፅ አስፈላጊነታቸውን መዘርዝር።
- በመካከላቸው ያለውን ልዩነት መናገር።
- ስዕል 2 ላይ ያለውን በማሳየት ከሰው ልጅ ክብር ጋር ያለውን ግንኙነት መግለጽ።

## ሐ. ማጠናከሪያ

- ከዚህ በላይ የተማሩዋቸውን አበይት ጉዳዮች ማለትም የክብርን ምንነት ማስገንዘብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች(ቋሚ እና ተለዋዋጭ)፤ክብር የሚገኝባቸው መንገዶችን ተማሪዎችን ማስገንዘብ
- ቋሚ እና ከሁኔታዎች ጋር የሚቀየር ሰብአዊ ክብርን ለይተው በመግለፅ ተማሪዎች የሰው ልጅ ክብር በሚለው ፅንሰ ሃሳብ ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ መርዳት

## ክትትል እና ግምገማ

- የሰው ልጅ ሰብአዊ ክብር ምንነት እና አስፈላጊነት ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተማሪዎችን መጠየቅ፤
- ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል በተግባር 1.2 እና ተግባር 1.3 ሥር ያሉትን እንዲሰሩ ማገዝ፤
- የራሳቸውን ልምድ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- መጥፎ ባህሪይን ከመላበስ የተነሳ ሰብአዊ ክብርን ማጣት ለተማሪዎች ምን ስሜት እንደሚፈጥር መጠየቅ
- በማህበረሰብ ዘንድ መልካም ስነ ምግባር መኖር እና መልካም ተግባር መፈፀም ክብር በማስገኘቱ ምክንያት ምን እንደሚሰማቸው ተማሪዎችን መጠየቅ፤

# ትምህርት 1.3: መሠረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት

(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 8)

## 1.ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች፤

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን በመለየት ትገልፃለህ/ሽ፡፡

2. ይዘት

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብኣዊ ባህሪያት(ፍቅር፣ ርህሩህነት፣ ለጋሽነት፣ በጎ አድራጊነት፣ መልካምነት፣ ወንድማማችነት፣ ታጋሽነት፣ ሰላም፣ መከባበር እና ተፅዕኖ አለማድረግ)

3. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

መምህራን፡- በመጀመሪያ ተማሪዎች ስለሰብአዊነት እንዲገነዘቡ እና መሰረታዊ ከሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ይገባል፡፡ ተማሪዎች በእያንዳንዱ መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን በተግባር እንዲለማመዱ አሳዩአቸው፡፡ ፍቅርና መግባባት ለሰዎች በሰላም ለመኖር የሚደግፉ ናቸው፡፡ ፍቅር፣ መግባባት እና ርህሩህነት እርስ በርስ የሚያስተሳስሩ ሲሆኑ ሲለያዩ ደግሞ ስሜትንና ልብን የሚሰብር ወይም የሚጎዳ መሆኑን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

**"ርህሩህነት"** መሰረታዊ ከሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት መካከል አንዱ ሲሆን በሁለት መንገድ የሚገለፅ ነው፡፡ አንደኛው የሌሎች ሰዎችን ችግር እና ጉዳት በትክክል በመረዳት ለመደገፍ ፍላጎትን ማሳየት

የሚል ነው። ይህ የተቸገሩ ሰዎች መረዳት የሚገባቸው በመሆኑ ለመርዳት ፍላጎት ማሳየትን ያካትታል። ሁለተኛው ደግሞ የሰዎችን ችግር እና ጉዳት በመረዳት እና ችግራቸውን ለመፍታት ተነሳሽነት መኖር ነው። ይህ በስሜት እና በመፈለግ ብቻ የሚከናወን ሳይሆን በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች በተግባር መርዳትን ያካትታል።

**"ለጋሽነት"** የፍቅር ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን ራስን ከመውደድ አልፎ ለሌሎች ሰዎች በተግባር መውደድን መግለጽን ይጨምራል። በሌላ መንገድ ለጋሽነት  የታመሙ ሰዎች፤ በጣም ድሃ የሆኑ እና የተጎዱ ሰዎችን ገንዘብ በመስጠት መርዳት ነው። በጎ አድራጎት የሚባለው በተግባር የሚገለጽ ሲሆን ይህም ጊዜውንና ችሎታውን መሥዋዕት በማድረግ  ያለምንም ክፍያ (ውጤት) ለሌሎች ሰዎች ጥቅም ማዋል ማለት ነው። ይህ ማለት ግን  ሀብቱን በሙሉ ለዚህ ጥቅም ማዋል ማለት አይደለም። ያለምንም ክፍያ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጊዜአቸውን እና ጉልበታቸውን ለማህበረሰቡ ጥቅም  ማዋል ማለት ነው።

**'መልካምነት"** ለሌሎች ሰዎች ጥሩ የሆነ አመለካከት እና መልካም ስነምግባር ለሌሎች ሰዎች ማሳየት ነው። መልካምነትን የምንገልፀው የሌሎች ሰዎችን ፍላጎት፣ ሃይማኖት እና ማንነት እንደራሳችን አድረገን በማክበር፣ ቦታ በመስጠት እና በመሳሰሉት ይገለጻል።  ለምሳሌ መልካም እና ወጥ የሆነ ባህሪይ መልካምነትን ይገልጻል።

**“ወንድማማችነት”** ስንል የግለሰቦች በመግባባት መተሳሰር ሲሆን ይህም የወንድማማችነት እና እህታማማችነት ስሜት ሆኖ የጋራ ዓላማ እና ፍላጎትን መሰረት በማድረግ የሚመሰረት ነው፡፡ በተጨማሪም ወንድማማችነት በአንድ ፋብሪካ ውስጥ በጋራ የሚሰሩ ሰራተኞች ወይም በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ አብረው የሚማሩ ተማሪዎች መሃከል በሚፈጠር መልካም ግንኙነት ሊገለጽ ይችላል፡፡

**“ታጋሽነት”** ማለት ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ያለምንም ተቃውሞ የታቀደው ነገር እስኪፈፀም ድረስ መጠበቅ ማለት ነው፡፡ ታጋሽ መሆን አንድን የተፈጠረን መጥፎ ነገር በትግዕስት በመቀበል ወደሚቀጥለው ደረጃ መሻገር ማለት ነው፡፡ ይህ የሰብአዊነት ባህሪይ፣ ስሜትን በመቆጣጠር ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ማሸነፍን የሚያስተምረን ነው፡፡

**“ሰላም”** እንደአጠቃላይ የጓደኝነት እና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚገኝ የመግባባት ፅንሰ ሃሳብ ሲሆን የግጭት እና የጠላትነት ጎጂነትን የሚገልፅ ነው፡፡ ሰላማዊነት የሚጀምረው ከሌሎች ሰዎች ጋር ስንገናኝ ሰላምታ በመጠያየቅ ነው፡፡ ሰላምታ መጠያየቅ በሰዎች መካከል ሰላም እና መልካም ግንኙነት ለመገንባት እና ለማጠናከር ትልቅ ሚና አለው፡፡

ከበሬታ ደግሞ ለሌሎች ሰዎች ክብር እና ዋጋ የምንሰጥበት ሲሆን ይህም በተግባር እና በቃላት የሚገለፅ ነው፡፡ ሁሉም የሰው ልጆች

በየትኛውም ቦታ እና ጊዜ መከበር አለባቸው። ክብር ያለአድልዎ ተመጣጣኝና እኩል የሆነ አገልግሎት ለግለሰቦች መስጠት ሲሆን በተጨማሪም ያለውን ህግ እና ደንብ መሰረት በማድረግ ተግባራትን መፈፀም ማለት ነው። ማንኛውም ሰው በህግ እና በደንቡ መሰረት እኩል አገልግሎት ማግኘት ይገባዋል።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች :

- ሰዕል1.3 — 1.13 የሚገኙትን እንደ ቅደም ተከተላቸው በክፍል ውስጥ መጠቀም ፤
- ለሌሎች ሰዎች አርዓያ የሚሆኑ፤ በማህበርሰቡ ውስጥ መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን የሚተገብሩ

## 5. የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ ባህሪያት ላይ ውይይት እንዲያከሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ በተግባር ማሳየት እንዲችሉ ማድረግ።
- መሠረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ለማስተማር የሚረዱ የተለያዩ ተረቶች እና ትረካዎችን መጠቀም፤

## 6. የመማር እና ማስተማር ሂደት

ለትምህርቱ ዝግጅት ማድረግ

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ላይ መፃህፍትን ማንበብ፤
- የዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት

## 7. የትምህርትአቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ለተማሪዎች መግለፅ፤
- መሰረታዊ የሆኑ የሰብአዊ ባህሪያት ዓላማዎችን ለተማሪዎች መግለፅ፤
- በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የተቀመጡትን የግንዛቤ ጥያቄዎች እያንዳንዱን መጠየቅ፤
- በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የተቀመጡትን መሰረታዊ የሆኑ የሰብአዊ ባህሪያትን የሚገልጹ የትምህርት ይዘቶችን ተማሪዎችን መጠየቅ፤

### ለ. አቀራረብ

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ምንነት መግለፅ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን በተሰጣቸው ክፍለ ጊዜ መሰረት መግለፅ፤
- የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን በተለየ መልኩ ያለውን መሰረታዊ ባህሪይ በጥልቀት መግለፅ፤
- በእያንዳንዱ ሰብአዊ ባህሪያት ላይ በተማሪዎች መፅሐፍ እና በሌሎች ጽሑፎች የተቀመጡትን ምሳሌዎች በመውሰድ መግለፅ፤

- በመጽሃፎቹ ውስጥ የቀረቡ ስዕሎች የሚያሳዩዋቸውን መሰረታዊ ባህሪያት እና ያላቸውን ግንኙነት ከርዕሱ ጋር በማያያዝ ገለፃ መስጠት ፤

## ሐ. ማጠናከሪያ

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን አስመልክቶ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤ አጭር እና ግልፅ የሆነ ማስታወሻም መስጠት፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ላይ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ እና በኑሮአቸው ውስጥ በተጨባጭ ሥራ ላይ እንዲያውሉ መርዳት፤.

## መ. ክትትል እና ግምገማ

- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ላይ ተማሪዎች ገለፃ እንዲሰጡ መጠየቅ፤
- መሰረታዊ በሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት መካከል ያለውን ልዩነት እንዲለዩ መጠየቅ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ላይ ተማሪዎች በዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ያላቸውን ልምዶች ለክፍል ተማሪዎች እንዲገልጹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በመጥፎ ባህሪይ ምክንያት ክብር ማጣት ምን ስሜት እንደሚፈጥር ተማሪዎችን መጠየቅ፤

- መልካም ባህርይ በማሳየት እና ለማህበረሰቡ የሚገባውን አገልግሎት በመስጠት ምክንያት ምን ስሜት እንደሚፈጠር ተማሪዎችን መጠየቅ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ሥራ ላይ ማዋል ለምን እንደሚጠቅምና ሥራ ላይ አለማዋል ደግሞ ምን እንደሚጎዳ በደንብ መግለፅ ፣

**የምዕራፉ ተግባራት መልስ**

**ተግባር 1.1 የቡድን ሥራ**

አራት አራት አባላት ያለው ቡድን በማደራጀት ስዕል 1.1. በተግባር እንዲያሳዩ አድርግ/ጊ፡፡ በመቀጠልም ዓረፍተ ነገሮቹን ተራ በተራ ድምፅ በማሰማት እንዲያነቡ አድርጉ፡፡

**ተግባር 1.2 የቡድን ሥራ**

ሦስት ሦስት አባላት ያሉዋቸውን ቡድኖች በማደራጀት እንዲወያዩ አድርግ/ጊ፡፡ በመቀጠልም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ አድርግ/ገ፡፡

1. ለሰው ልጅ የሚሰጠው ክብር እንደ ተጨባጨ ሁኔታው ተለዋዋጭ ነው፡፡ ክብር የሚያስገኘው ተግባር በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያለውና ክብር የማያስገኘው ደግሞ በተቃራኒው ክብር የማያስገኝ ነው፡፡
2. በማህበረሰቡ ውስጥ ክብር ከሚያሳጡ ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹ፤

    ሀ. ለራስ ክብር አለመስጠት፣ ራስን አለማክበር፤

ለ. ጥሩ የሆነ ባህሪይ ማጣት፤

ሐ. ከባህል ውጪ በሆኑ ሥራዎች ላይ መሰማራት፤ ለምሳሌ፡ ስርቆት፣ መዋሸት፣ ታማኝ አለመሆን፣ ሙሰኝነት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ተግባር 1.3 የግል ስራ**

1. በአከባቢያቸው ትልቅ ክብር ያላቸውን ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው ክብር ያገኙበትን ምክንያት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡
2. ክብር የማያስገኙ ባህርያት ደግሞ ውርደት፣ ራስን መጥላት፣ ከማህበረሰቡ ራስን ማግለል፣ የበታችነት እና የመሳሰሉት ስሜቶች ናቸው፡፤

**1.4 የግል ሥራ**

1. ለሰው ልጅ ክብር መስጠት የተለያዩ ጥቅሞች አሉት፡፡ እነሱም፡
   - ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤
   - ለሰዎች እርዳታ ለመስጠት ይረዳል፤
   - የሰው ልጅ በተፈጥሮ ያገኘው መብት እንዲከበር ያደርጋል፡፡
2. ተማሪዎች የሰው ልጅ ክብር ላይ ያላቸውን ልምድ (በግል፣ በቤተሰብ፣ በጎረቤት፣ ከጓደኞች፣ በሥራ ቦታ፣ በሀገር እና በመሳሰሉት) እንዲያካፍሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች አባቴን፣ እናቴን፣

ወንድሜን፣ እህቴን እወዳቸዋለሁ በማለት ለቤተሰቦች ክብርን እንዲያሳዩ ማድረግ፤

## ተግባር 1.5 የግል ሥራ

1. ለያንቱ፣ በሪሶ እና ዱሬቲ የሚለውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ ከሦስቱ ልጆች የዱሬቲ የተሻለ መሆኑን ከነምክንያቱ እንዲገልፁ አድርግ/ጊ። ይህም ዱሬቲ ሰውን የሚትወደው ጥቅምን መሰረት በማድረግ ሳይሆን በሰብአዊነት ላይ በመመስረት መሆኑን እንዲናገሩ አድርግ/ጊ።
2. ከዚህ በላይ የተገለፀው ሀሳብ ከለያንቱ፣ በሪሶ እና ዱሬቲ የተለየ እና የተሻለ መሆኑን እንዲረዱ አድርግ/ጊ።

## ተግባር 1.6 የግል ሥራ

ተማሪዎች በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ በስዕል 1.4 የቀረበውን በማየት የተረዱትን እንዲገልፁ አድርግ/ጊ። በሀ ስር ያሉት ተጣልተው እንዳዘኑ እና በ ለ ስር ያሉት ደግሞ አብረው እየተጫወቱ እና እየተደሰቱ መሆኑን እንዲሁም የተቃቀፉበት ሁኔታ ደስታን የሚገልፅ መሆኑን እንዲያስረዱ አድርግ/ጊ።

## ተግባር 1. 7 የግል ሥራ

1. ሲንቦ ጓደኛዋና ቦንቱን እንዳፅናናቻት ተማሪዎችም ጓደኞቻቸውን ማፅናናትን በሚመለከት ሃሳብ መስጠት እንዲችሉ አበረታቷቸው።

2. አዎ። ምክንያቱም ተማሪዎች እርስ በርስ በመመካከር በተጨማሪም የወላጆች፣ የመምህራን እና የሌሎች ትላልቅ ሰዎችን ምክር የሚፈልጉ ስለሆነ ነው።

## ተግባር 1.8 የቡድን ሥራ

1. ርህሩህነት በተለያዩ ተግባራት ይገለፃል። ለምሳሌ በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች በሚፈልጉት ነገር ከጎናቸው መቆም፤ የሌሎችን ሰዎች ችግር እና ጉዳት በትክክል በመረዳት ሌሎች ሰዎችም እንዲረዱአቸው ማድረግ እና የመሳሰሉ ሃሳቦችን ማንሳት እንዲችሉ ማድረግ ነው። .
2. ከላይ እንደተገለፀው ተማሪዎች ከርህሩህነት አንጻር ራሳቸውን እንዲያዩ እና እንዲገመግሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። በቡድን ሀሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ በመጨረሻም ልምዳቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማበረታታት ነው። ለምሳሌ በክፍል ውስጥ እና በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ችግር ቢያጋጥማቸው እንዴት መረዳዳት እንደሚችሉ እንዲገልፁ ማድረግ ይቻላል።

## ተግባር 1.9. የግል ሥራ

ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ቤተሰብ፣ ጓደኛ እና የመሳሰሉትን በመጠየቅ እርስ በርስ እንዲወያዩበት ማበረታታት ነው።

## ተግባር 1.10

1. በጨዋታ መሃል ጓደኛህ ቢወድቅ ምን በማድረግ ትረዳዋለህ? ለምሳሌ፤ የወደቀውን ማንሳት እንዳለባቸው፣ ሰውን ገፍትሮ መጣል እንደሌለባቸው መገንዘብ እንዲችሉ ማበረታታት ነው፡፡
2. ተማሪዎች በምን ሁኔታ ክብርን እንደሚገልፁ ያላቸውን ልምድ እንዲነጋገሩ አበረታታቸው፡፡ ለምሳሌ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በጎረቤት ወዘተ አካባቢ የሚታዩ የከበሬታ ልምዶችን አስመልክተው የገጠማቸውን ሃሳብ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡

## ተግባር 1.11 የግል ሥራ

1. በወንድማማችነት ስሜት መግባባት እና አንድነት ያላቸው መሆኑን፤
2. ወንድማማችነት የመግባባት፤ የመፈቃቀር፣ የመረዳዳት፣ የመተሳሰብ እና የመሳሰሉት ጥቅሞች አለው፡፡

## ተግባር 1.12 የግል ሥራ

1. ተማሪዎች መምህራን በሚያረፍዱበት ጊዜ በትግዕስት እና በፀባይ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለው መጠበቅ እንዳለባቸው፤ ትዕግስተኛ መሆን እና በማይመች ሁኔታ ውስጥ ያለምንም ተቃውሞ የታቀደው ነገር እስኪከናወን ድረስ በትግዕስት መጠበቅ ነው፡፡
2. ተማሪዎች በክፍላቸው ተጨባጭ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በተግባር እንዲያሳዩ መፍቀድ ነው፡፡ መምህራቸው አርፍዶ

ወደ ክፍል ቢመጣ ምን ይሰማቸዋል? ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ያላቸውን ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ ነው፡፡

**ተግባር 1.13 የቡድን ሥራ**

**ተላላፊ በሽታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ሰላምታ ከመለዋወጫ ዘዴዎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡- እጅ ማወዛወዝ፣ በክርን መነካካት፣ እጅ ወደላይ ማንሳት እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡**

**የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍል I: እዉነት ሀሰት** **ክፍል II: አዛምድ**

**ክፍል III: ምርጫ**

1. እውነት 1. ለ
1. መ
2. ሐሰት 2. ሀ
2. ሐ
3. እውነት 3. መ
3. ለ
4. እውነት 4. ሠ
5. ሐሰት 5. ሐ

IV. **ተማሪዎች በመማሪያ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር በቤታቸው እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡ተማሪዎች ልምምዳቸውን በተሻለ ሁኔታ በማከናወን ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡**

# ምዕራፍ 2: ሰዎችን ማክበር

**የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 20**

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ሰዎችን የማክበር ጽንሰሀሳብ ላይ ያተኩራል፡፡ ስለዚህ ሌሎች ሰዎችን የማክበር አስፈላጊነት፤ ለምሳሌ ታላላቆችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፤ የህብረተሰብ መሪዎችን፣ መምህራንን፣ ቤተሰብን፣ ጎረቤትን፣ ጋደኞችን እና የመሳሰሉትን ማክበርን ያጠቃልላል፡፡ ሌሎች ሰዎችን የሚያከብሩ ግለሰቦችን ባህሪያትም ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ችግሮችን ያካትታል፡፡

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- ✓ ሰዎችን የማክበር ምንነትን ይገልፃሉ፤
- ✓ ሌሎች ሰዎችን የማክበር  አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፤
- ✓ የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ እና ፍላጎት ያደንቃሉ፤
- ✓ የሚከበሩ ሰዎችን ባህሪያት ያሳያሉ፤ ¡
- ✓ ካለመከባበር ሊመጡ የሚችሉ ችግሮችን ይለያሉ፡፡

## 2.1: ሰዎችን ማክበር

**(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 12)**

1.ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ ዝቅተኛ  የመማር ብቃቶች፤

- ✓ ለሰው ልጅ የሚገባውን ክብር ይለያሉ፤
- ✓ ተማሪዎች ለክፍላቸው ያላቸውን ክብር ያሳያሉ፡፡

## 1. ይዘት

- ሰዎችን ማክበር

## 2. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

ሰዎችን ማክበር የሚጀምረው ራስን ችሎ መኖር፣ ከሌሎች ጋር ያለንን ልዩነት መቀበል እና ነፃነት ያለን መሆናችንን ከመቀበል ነው፡፡ ሰዎችን ማክበር የግለሰቦችን ክብር ማግኘት ተገቢነት ከመቀበል ይጀምራል፡፡ ሰዎችን ማክበር ማለት ለሰው ልጅ ክብር እና ዋጋ መስጠት ማለት ነው፡፡ ሰዎችን ማክበር ለአክባሪውም ሆነ ለተከባሪው ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

መከባበር የሰዎችን ግንኙነት ያጠናክራል፡፡ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ባህሪይ ማስተካከል እና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ ሃላፊነት መውሰድ አለባቸው፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ አብረው የሚማሩ ተማሪዎች በሙሉ ጓደኛሞች ናቸው፡፡

## 3. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለውን እና ሌሎችንም መጠቀም ይገባል፡፡ ለምሳሌ የአረጋዊያንን፣ የሃይማኖት አባቶችን እና የመሳሰሉትን ሥዕሎች ማሳየት ይቻላል፡፡

በትክክለኛ ሞዴል መጠቀም፤ የተከበሩ አረጋዊያንን ወደ ክፍል በመጋበዝ ወይም ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙትን አረጋዊያን እንዲጎበኙ መርዳት በትምህርቱ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡

## 4. የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ተማሪዎችን በቡድኖች በመክፈል ሰዎችን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው? በሚለው ጥያቄ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፤
በተረት፣ በሚና ጨዋታ፣ ወዘተ.ክብርን እንዴት እንደሚተገበር ማለማመድ ይገባል፡፡

## 5. የመማር ማስተማር ሂደት

- የቡድን ውይይት፣
- ገለፃ፣
- ጥያቄና መልስ፣

## የትምህርቱ ቅድመ ዝግጅት

- ✓ ስለ ሰው ክብር ፅንሰ ሃሳብ የሚገልጸውን ጽሑፍ ማንበብ፤
- ✓ በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለውን ማስገንዘብ፤
- ✓ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት

7. የትምህርቱ አቀራረብ

**ሀ) መግቢያ**

-ሰዎችን ማክበር የሚለውን ርዕስ ማስተዋወቅ፤
- የትምህርቱን ዓላማ መግለፅ፤
- በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያሉትን የግንዛቤ ጥያቄዎች
መጠየቅ፤

**ለ) አቀራረብ**

- የይዘቱን ትርጉም መግለጽ እና አጭር ማብራሪያ መስጠት፤
- በእያንዳንዱ ስዕል ላይ ገለፃ መስጠት፡፡

## ሐ) ማጠናከሪያ

- የሰው ክብር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲረዱ መርዳት፤
- ሌሎች ሰዎችን ማክበር የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ተረድተው ሥራ ላይ እንዲያውሉ መርዳት።

መ) ክትትል እና ግምገማ

- ሰዎችን ማክበር ምን እንደሆነ እንዲያብራሩ ተማሪዎችን መጠየቅ፤
- አረጋዊያንን፣ የሃይማኖት አባቶችን እና የተለያዩ የማህበረሰብ አካላትን እንዴት እንደሚያከብሩ መጠየቅ፤
- ተማሪዎችን በቡድኖች በመክፈል የተሰጣቸውን ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ፤
- ተጨባጭ የሆኑ የአኗኗር ሁኔታዎችን እንዲያሳዩ ማድረግ፤
- ለሰዎች እንዴት ክብር እንደሚሰጥ ያላቸውን ልምድ ክፍል ውስጥ እንዲለዋወጡ ማድረግ፤ .

## 2.2: ሰዎችን የማክበር አስፈላጊነት

**(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 8)**

1.ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች፤

- ✓ የሰው ልጅን ማክበር ለምን እንደሚያስፈልግ ትለያለህ፤
- ✓ በአከባቢያችው የሚገኙ አረጋዊያንን እና የተከበሩ ሰዎችን ትዘረዝራለህ፤
- ✓ አረጋዊያንን እንዴት እንደምናከብር በክፍል ውስጥ በተግባር ታሳያለህ/ሽ፡፡

**1. ይዘት**

- ሌሎች ሰዎችን ማለትም አረጋዊያንን፣ ታላላቆችን፤ የሃይማኖት አባቶችን፤ ቤተሰብን፤ ጎረቤትን እና የክፍል ተማሪዎችን የማክበር ጠቀሜታ፤

**2. አጭር አጠቃላይ መግለጫ**

ሌሎች ሰዎችን ማክበር የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡

- የማህበረሰብን ግንኙነት ያጠናክራል፤
- የደስታ እና የፍቅር ስሜት እንዲኖር ያደርጋል፤
- እኩልነት እና ሰላም እንዲኖር ያደርጋል፤
- በማህበርሰቡ መሃከል የመረዳዳት ስሜት እንዲጠናከር ወዘተ.ያደርጋል፡፡

አረጋዊያን የሚባሉት በእድሜያቸው የገፉ ሰዎች ናቸው። ለምሳሌ እናት እና አባት፣አያት እና ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የተከበሩ ሰዎች የሚባሉት አረጋውያን ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ በድርሻቸው እና በተግባራቸው የሚታወቁ ሰዎች ናቸው። በማህበረሰቡ ውስጥ በድርሻቸው እና በተግባራቸው የሚታወቁ ሰዎች የሚባሉት የሃይማኖት አባቶች፣ የህብረተሰብ መሪዎች፤ አባገዳዎች፣ ሃደ ሲቄዎች እና የመሳሰሉት ናቸው።

## 3. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ታላላቆችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ መምህራንን፣ የክፍል ተማሪዎችን፣ ጎረቤቶችን እና የመሳሰሉትን የሚያሳይ ስዕል፤
- በጭውውት፣ በማህበረሰብ ውስጥ አርዓያ መሆን የሚችልን ሰው በማሳየት።

## 4. የመማር ማስተማር ዘዴ

- ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ሰዎችን የማክበር ጠቀሜታ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፤
- በጭውውት መልክ ሰዎችን ማክበርን እንዲለማመዱ ማድረግ፤

## 5. የመማር ማስተማር ሂደት

**ዝግጅት**

- ✓ ሰዎችን ለማክበር ስለ ሰዎች ክብር የሚገልጸውን ጽሑፍ ማንበብ፤
- ✓ በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ላይ የሚገኘውን ስዕል ማስገንዘብ፤
- ✓ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት፤

## 6. የትምህርትአቀራረብ

### ሀ) መግቢያ

- ሰዎችን የሚያከብር ሰው መገለጫዎች የሚለውን የትምህርቱን ይዘት ማቅረብ፤
- የትምህርቱን ዓላማ ማቅረብ፤
- የቀረቡትን የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ፤
- የትምህርቱን ይዘት እንዲገነዘቡ ማድረግ፤

ለ) አቀራረብ

- የክብርን ትርጉም ማስረዳት እና ገለፃ መስጠት፤
- በእያንደንዱ ስዕል ላይ ገለፃ መስጠት፡፡

### ሐ) ማጠናከሪያ

- ለሰዎች ትክክለኛውን ክብር መስጠት ግዴታ መሆኑን፣ ከሰዎች ጋር በሰላም መኖር አስፈላጊ መሆኑን፣ ክብር አሰጣጥን በተግባር በማለማመድ ወዘተ. የክብርን ጽንሰሀሳብ እንዲገነዘቡ ማድረግ፤

## መ) ክትትል እና ግምገማ

- ሰዎችን ማክበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልፁ መጠየቅ፤
- አረጋዊያንን፣ የሃይማኖት አባቶችን እና የተለያዩ የማህበርሰብ አካላትን እንዴት እንደሚያከበሩ መጠየቅ፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የተሰጧቸውን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤
- ተጨባጭ የሆነ የአኗኗር ሁኔታን ፅንሰ ሃሳብ እንዲገልፁ ማድረግ፤
- ለሰዎች ክብር የሚሰጥበት ሁኔት ላይ ያላቸውን ልምድ በክፍል ውስጥ እንዲለማመዱ ማድረግ፤

ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ያለውን ተግባር እንዲሰሩ መርዳት፤

## 2.3: የተከበሩ ሰዎች የሚታወቁባቸው ባህሪያት

### 1.ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤

- የተከበሩ ሰዎች የሚያሳዩዋቸውን ባህሪያት ይገልፃሉ፡፡

1. **ይዘት**
    - የተከበሩ ሰዎች የሚታወቁባቸው ባህሪያት
2. **አጭር አጠቃላይ መግለጫ**

   ለሌሎች ሰዎች ክብር የሚሰጡ ሰዎች ሁሉ የተከበሩ ናቸው፡፡ በትምህርቱ ውስጥ ቤተሰብ፣ ጎረቤት፣ መምህራን፣ ጓደኞች፣ አረጋዊያን እና የሃይማኖት አባቶች መከበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት፤

   የተከበሩ ሰዎች የሚታወቁባቸው ባህሪያት አሏቸው፡፡የተከበሩ ሰዎች ጥሩ ፀባይ ያላቸው ፤ ሰዎችን የሚያስተናግዱ፤ ተጠያቂነትን የሚወስዱ፣ የማህበረሰቡን ባህል እና እሴት የሚያከብሩ፤ የተጣሉ ሰዎችን የሚያስታርቁ፤ ታጋሽ የሆኑ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. **የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**
    - የተከበሩ ሰዎች ባህሪያትን የሚያሳየውን ስዕል 2.9 ለተማሪዎች ማሳየት፤
    - በማህበረሰቡ ውስጥ አርዓያ የሚሆኑትን ሰዎች በመወከል በጭውውት መልክ ማሳየት፡፡

4. **የመማር ማስተማር ዘዴ**

- ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት፡፡ የተከበሩ ሰዎች ባህሪያት በሚለው ጽንሰሃሳብ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፤

- ሁለት ሁለት በመሆን ተማሪዎች የተከበሩ ሰዎች ባህሪያትን እንዲገልፁ ማድረግ፤

- በሚና ጨዋታ እና በጭውውት የተከበሩ ሰዎች ባህሪያት ምን እንደሆኑ እንዲለዩ ማድረግ ይቻላል፡፡

5. **የመማር ማስተማር ሂደት**

**ቅድመ ዝግጅት**

- ✓ የተከበሩ ሰዎች የሚታወቁባቸውን ባህሪያት የሚገልጸውን ጽሑፍ ማንበብ፤
- ✓ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የሚገኙትን ስዕል ማስገንዘብ፤
- ✓ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- ✓ የተከበሩ ሰዎች ባህሪያትን በደንብ ማንበብ፤
- ✓ የተከበሩ ሰዎች ልምዳቸውን ለተማሪዎች እንዲያካፍሉ መጋበዝ ናቸው፡፡

## 6. የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

- የተከበሩ ሰዎች ባህሪያት የሚለውን ይዘት ማስተዋወቅ፤
- የትምህርቱን ዓላማ መግለፅ፤
- በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ላይ የተገለፀውን የተግባር ጥያቄ መጠየቅ፤

**ለ)** አቀራረብ

- ሰዎችን የማያከብሩ ሰዎች ባህሪያትን መግለፅ

**ሐ)**ማጠናከሪያ

ሰዎችን የማያከብሩ ሰዎች ባህሪያት ላይ ማተኮር

**መ) ክትትል እና ግምገማ**

- የተከበሩ ሰዎች የሚያሳዩዋቸው ባህሪያት ምን እንደሆኑ መጠየቅ፤
- አረጋዊያን፣ የሃይማኖት አባቶች እና የተለያዩ የማህበርሰብ ክፍሎች እንዴት እንደሚከበሩ መጠየቅ፤
- ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የተሰጧቸውን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤
- ለሰዎች ክብር እንዴት እንደሚሰጥ ያላቸውን ልምድ በክፍል ውስጥ ማለማመድ ነው፡፡

## 2.4: ሰዎችን ካለማክበር የሚከሰቱ ችግሮች

**.ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤**

- ለሰዎች ክብር ካለመስጠት የሚመጡ ተፅዕኖዎችን ይለያሉ፡፡

1. **ይዘት**
   - ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎች
2. **አጭር አጠቃላይ መግለጫ**

ሰዎችን የማክበር ተቃራኒ ሰዎችን መናቅ ነው፡፡ መናቅ ለአንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ክብር አለመስጠት እና ጥቅም እንደሌለው መቁጠር ነው፡፡ ሰው መናቅ ማለት ስሜት፣ ፍላጎት፣ ክብር፣ ለሰብአዊነቱ እና ለማህበራዊ ህይወቱ ትክረት አለመስጠት ወዘተ. ነው፡፡ ሰው የመናቅ መገለጫዎች ስድብ፣ በመጥፎ ተግባር እና ባህሪይ ሰዎችን መቀበል ወዘተ. ናቸው፡፡

አለመከባበር የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያመጣል፡፡

ከእነዚህም መካከል ጥቅቶቹ፤

- የጓደኝነት ስሜትን ያጠፋል፤
- የሰዎችን ክብር ይጎዳል፤
- ከሰዎች ጋር መግባባትን ይቀንሳል፤
- ተቻችለው አብሮ መኖርን ይጎዳል፡፡

3. **የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች**

- ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎችን የሚያሳዩሥዕሎች
- ሚና ጨዋታ: በማህበረሰብ ውስጥ አርዓያ መሆን የሚችሉ ሰዎችን ወክሎ ማሳየት፡፡

4. **የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- የቡድን ውይይት፤
- ገለፃ፤
- ጥያቄ እና መልስ፤

5. **የመማር ማስተማር ሂደት**

**ቅድመ ዝግጅት**

- ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎችን የሚያሳይ ሂደት፤
- ተማሪዎች ባላቸው ግንዛቤ ላይ እንዴት ሃሳብ መስጠት እንደሚችሉ ማመቻቸት፡፡

6. **የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

- ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎች የሚለውን ርዕስ ማስተዋወቅ፤
- የትምህርቱን ዓላማ መግለፅ፤
- በተማሪዎች መፅሐፍ የተካተቱትን የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ፤

- ሰዎችን በማክበር እና ባለማክበር መሃከል ያለውን ልዩነት እንዲገመግሙ ማድረግ፤

**ለ. የትምህርቱ አቀራረብ**

አለመከባበር የሚያመጣቸው ተፅዕኖዎች ምን ምን እንደሆኑ መግለፅ፤

**ሐ. ማጠናከሪያ**

ሰዎችን ካለማክበር በሚመጡ ተፅዕኖዎች ላይ የተሰጠውን ትምህርት ማጠናከር

**መ. ክትትል እና ግምገማ**

ተማሪዎች ትምህርቱን መገንዘባቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለው በቴስት እና በአሳይንመንት ሊሆን ይችላል፡፡

- የተሰጠውን ትምህርት በጥሩ ሁኔታ ለመረዳት እንዲረዳቸው የቤት ሥራ መስጠት ይቻላል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በውይይት ላይ እንዲሳተፉ ለሁሉም የቡድን ሥራ መስጠት

## የምዕራፍ ሁለት የተግባር ጥያቄዎች መልስ

## ተግባር 2.1 የግል ሥራ

1. ሰላምታ መለዋወጥ፣ መልካምነት፣ ማመስገን፣ መታዘዝ እና የመሳሰሉትን ማለት እንዲችሉ ማበረታታት፤
2. የመደሰት፣ የመከባበር፣ አቀባበል የማድረግ፣ የማመስገን ስሜት እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## ተግባር 2.2 የግል ሥራ

ተማሪዎች የተጠየቁትን ጥያቄ በምን መልኩ እንደሚመልሱ ግብረ መልስ መስጠት እና ታላላቆችን ማክበር እንዳለባቸው አጠናክሮ መግለፅ፤

## ተግባር 2.3 የግል ሥራ

1. ልጆች ከመቀመጫቸው ተነስተው ትላልቅ ሰዎችን ሲያስቀምጡ፤
2. በአከባቢያቸው ማህበርሰቡ አረጋዊያንን እንዴት እንደሚያከብር በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተጨማሪ ሃሳብ መስጠት፤

## ተግባር 2.4 የቡድን ሥራ

ተማሪዎች የሃይማኖት አባቶችን ማክበር ያለው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንዲወያዩበት አግዟቸው፡፡ ለምሳሌ ሰዎችን ማክበር ጤናማ የሆነ ኑሮ ለመኖር፤ መልካም የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር፤ መዋደድና ጥሩ ስነምግባር ለማዳበር እና የመሳሰሉት ጥቅሞች አለው፡፡ እንዲሁም በጓደኞች፣ በቤተሰብ እና በህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ያገለግላል፡፡

## ተግባር 2.5 የግል ሥራ

1. መምህራንን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን፤
2. መምህራን ወደ ክፍል ሲገቡ ተነስተው በክብር መቀበል፤ የትምህርቱን ክፍለ ጊዜ በትክክል መከታተል፤ የክፍል

እና የቤት ስራን ጠንክረው መስራት፤ የትምህርት ቤት ሰዓት ማክበር፤ የመምህራንን ምክር መከታተል፡፡

**ተግባር 2.6 የግል ሥራ**

1. ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸውንና የክፍል ጓደኞቻቸውን የሚያከብሩ መሆናቸውን በተለያዩ ጉዳዮች ይገልጻሉ፡፡ መላላክ፣ መታዘዝ፣ ምክርን መቀበልና መተግበር፣ ማክበርና መውደድ እና የመሳሰሉትን ለክፍል ተማሪዎች እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
2. ቤተሰብን ማክበር በሰላምና በመግባባት መኖርን፣ እሴትን መጠበቅን፣ ያሰቡት ቦታ መድረስን፣ክብር ማግኘትን፣ በቤተሰብ እና በራስ መተማመን ማግኘትን፣ ማህበራዊ ኑሮ ማጠናከርን ያካትታል፡፡

**ተግባር 2.7 የግል/የቡድን ሥራ**

1. ጎረቤቶችን የምናከብርባቸው መንገዶች፡ ሰላምታ መለዋወጥ፣ በችግር ጊዜ መረዳዳት፣ ደስታን በጋራ መካፈል፣ ከጎረቤትና ጓደኛ ጋር መልካም ቀረቤት መፍጠር ናቸው፡፡
2. በጥንድ በመሆን ከላይ የተገለጹትን ጉዳዮች በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ ነው፡፡
3. ጎረቤቶችን ማክበር ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር፣ ለመከባበር፣ ለመዋደድ፣ አንድነት

**ለመፍጠር እና ለመሳሰሉት የሚጠቅም መሆኑ ናቸው፡፡**

**ተግባር 2.8 የግል ሥራ**

ሰላምታ መጠያየቅ፣ አብሮ መጫወት፣ በጋራ መወያየት፣ በችግር ጊዜ መረዳዳትና መመካከር፣ ደስታን በጋራ መካፈል እና የመሳሰሉትን እንዲናገሩ ማድረግ፤

**ተግባር 2.9 የግል ሥራ**

1. የተከበሩ ሰዎች ከሚታወቁባቸው ባህሪያት መካከል በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ይዘት 1.3 ስር የተቀመጡትን እና ሌሎችንም በመጨመር እንዲዘረዝሩ ማድረግ፤
2. ከተዘረዘሩት ባህሪያት ውስጥ የራሳቸው የሆነውን ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ፤

**ተግባር 2.10 የቡድን ሥራ**

1. ተማሪዎችን በቡድን ካደራጀህ/ሽ በኋላ ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ጉዳቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም ጊዜ በይዘት 2.4. ስር የተዘረዘሩትን እንዲያነሱ ማድረግ፤
2. ሰዎችን ማክበርን ወይም አለማክበርን አስመልክቶ በይዘት 2.4. ስር የተዘረዘሩትን በትኩረት በማንሳት እንዲረዱ ማድረግ፤

**የምዕራፍ 2 የክለሳ ጥያቄዎች መልስ**

**I. እውነት/ሐሰት**

1. ሐሰት 2. እውነት 3.እውነት 4.እውነት 5.ሐሰት

**II. ምርጫዎች**

1.ሐ 2.ለ 3.መ

**III. አጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. ትላላቆችን ከምናከብርባቸው መንገዶች መሃከል፤

- ከአረጋዊያን ጋር ስትገናኝ ማክበር፣
- ምክራቸውን በትክክል ማዳመጥ፤
- አረጋዊያን በሚያወሩበት ጊዜ አለማቋረጥ ወዘተ.

በጥያቄ 1 እና 2 ለተነሱት ሃሳቦች በይዘት 2.2. እና 2.4 ሥር የተገለጸጹትን በደንብ እንዲመለከቱ ማድረግ ይገባል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፡ እኩልነት

የክፍለ ጊዜ ብዛት 20

*መግቢያ*

የተከበሩ መምህር/ት! ይህ ምዕራፍ የእኩልነትን ምንነት፣ በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ዘንድ ሊከበር ስለሚገባው እኩልነት ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡ እንደዚሁም እኩልነት የሚገለጽባቸው ጉዳዮች ማለትም የስርዓተ ፆታ፣ የቋንቋ ፣የሐይማኖት እና የባህል እኩልነት ናቸው፡፡ በመጨረሻም የእኩልነት አመለካከት አስፈላጊነትና እኩልነት ባለመኖሩ ምክንያት ሊመጡ ስለሚችሉ ጉዳቶች ያስተምራል፡፡

የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤት

- የእኩልነትን ምንነት መግለፅ፤
- የእኩልነትን አስፈላጊነት መግለፅ፤
- በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ዘንድ ፍትሐዊ ድርጊትን ማሳየትና፤
- የእኩልነት አለመኖር የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች መለየት ናቸው፡፡

## 3.1. የእኩልነት ምንነት

የተመደበለት ክ/ጊዜ 4

1.ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤

- የእኩልነትን ምንነት ይገልፃሉ፡
- በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሊያገኟቸው የሚገቡ መብትና ጥቅሞችን ይለያሉ፡፡

1. **የትምህርት ይዘት**

- የእኩልነት ምንነት
- እኩልነትን የሚያንፀባርቁ ተግባራት

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

- ለመጀመሪያ ጊዜ እኩልነት የሚለውን ቃል ስትሰማ/ሚ ምን አይነት ሀሳብ ወደ አእምሮህ /ሽ ይመጣል?
- እኩልነት ምንድን ነው?

የተከበሩ መምህር/ት! ከዚህ በላይ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ስለዚህ ተማሪዎ ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡መልሳቸው ካለፈው ትምህርት ምን እንደተረዱ ለመለየትና ለአዲሱ የትምህርት ርዕስ ራስን ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡

## 2. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

- ይህ ትምህርት የእኩልነትን ምንነት እንዲያውቁ ለመርዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም ስለ እኩልነት ምንነት ሲወያዩ የራሳቸውን ልምድ እንዲገመግሙ ያስችላቸዋል፡፡
- የእኩልነት መብት በዘር፣ በሐይማኖት ፣ በፆታ ፣ በቋንቋ፣ በህብረተሰብ ኑሮ ደረጃና በመሳሰሉት ልዩነት ሳይፈጠር በተመሳሳይ ሁኔታ የሚታይ ነው፡፡

## 3. የትምህርት መርጃ መሳሪያ

እኩልነትን የሚያመለክቱ ፎቶዎች (ሰዎች አብረው ሲሰሩ ፣ ሲጫወቱ እና የመሳሰሉት)

## 4. የመማር ማስተማር ዘዴ

መምህር/ት፡- የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- እኩልነትን በተመለከተ የቤተሰብ ተግባር
- ለትምህርቱ መግቢያ
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ውይይት

5. **የመማር ማስተማር ሂደት**

**ቅድመ ዝግጅት፡**

- **ለትምህርቱ ምቹ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴና የትምህርት መርጃ መሳሪያ መምረጥ**
- **በዚህ ትምህርት ውስጥ የተነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን ለተማሪዎች ማሳወቅ፡፡**
- **በዚህ ጉዳይ ላይ የራሳቸውን አመለካከት እንዲለዋወጡ ማበረታታት፡፡**

6. **የትምህርቱ አቀራረብ**

ሀ. መግቢያ

- **በእኩልነት ምንነት ላይ በማተኮር የትምህርቱን መግቢያ በአጭሩ ለተማሪዎች ማቅረብ፡፡**
- **የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ማስተዋወቅ፡፡**
- **ተማሪዎች ስለ እኩልነት ካሁን በፊት ያላቸውን ግንዛቤ ወደዚህ ርእስ እንዲያመጡ ወይም እንዲያስታውሱ ማበረታታት፡፡**
- **የተማሪዎችን ሀሳብ ማነሳሳት የሚችሉ ጥያቄዎችን ማንሳት፡፡**
- **በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ መሃከል የሚከበሩ እኩልነቶች በምን ጉዳዮች ላይ እንደሆኑ በምሳሌ በመግለፅ ውይይት ማስጀመር**

## ለ. የትምህርቱ አካል

በተሰጠው ትርጓሜ ላይ በመመርኮዝ የእኩልነትን ምንነት እንዲረዱና እንዲለማመዱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማሳየትና መግለፅ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ተማሪዎች ስለ እኩልነት ምንነት ከአካባቢያቸው ተጨባጭ የሆነ ምሳሌ እንዲያቀርቡ ማበረታታት

## ሐ. ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ሀሳብ ለይተው እንዲያወጡ መጠየቅ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ያላነሷቸውን አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ነጥቦች በማንሳት ትምህርቱን ማጠናከር፡፡

## መ. ምዘና ፡

ተማሪዎች ትምህርቱን መገንዘባቸውን ማረጋገጥ፡፡ ይህ መሆን የሚችለው በሙከራ ጥያቄዎችና አሳይመነት ነው፡፡

## 3.2. እኩልነት በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ

የተመደበለት ክ/ጊዜ 7

1.ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤

- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን የእኩልነት መብት ይዘረዝራሉ፤
- ተማሪዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን የእኩልነት መብት ይገልፃሉ፡፡

### 1. የትምህርት ይዘት

እኩልነት በትምህርት ቤትና በህብረተሰብ ዘንድ ለምሳሌ፡

የቋንቋ እኩልነት፣ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት፣የሐይማኖት እኩልነትና የባህል እኩልነት

### 2. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

- ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ዘንድ እኩልነትን ማክበር እንዲቀጥሉ ማበረታታት፡፡
- ተማሪዎች ስለ ስርዓተ ፆታ፣ ቋንቋ፣ሐይማኖት እና ባህል እኩልነት ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ የእኩልነት መብታቸው እንደ ጥያቄ የመጠየቅ፣ መልስ የማግኘት ፣ በተጓዳኝ ትምህርት ውስጥ የመሳተፍና የትምህርት ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ

የመያዝና የመጠቀም እንዲሁም ከአድልዎ መጠበቅ መሆናቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ፡፡

**የስርአተ-ፆታ እኩልነት** ፡- ሴቶችና ወንዶች እኩል መብትና እድል ማግኘት

ነው፡፡

**የቋንቋ እኩልነት**፡- በአለም ላይ ያሉ ቋንቋዎች ሁሉ አገልግሎት በመስጠት

እኩል ናቸው፡፡

**የሐይማኖት እኩልነት** ፡- ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን ሐይማኖት

የመከተል፣የማስተማርና የመስበክ መብት አለው፡፡

**የባህል እኩልነት** ፡- አገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ባህል

አሏት፡፡ማንኛውም ባህል ከሌላ ባህል አይበልጥም፤ አያንሰምም፡፡

3. **የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

ወንዶችና ሴት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በእኩልነት የተለያዩ ስራዎችን ሲሰሩ የሚያሳይ ፎቶ ማሳየት፡፡

## 4. የመማር ማስተማር ዘዴ

- የቡድን ውይይት
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ

## 5. የማስተማር ሂደት

- የእኩልነትን ምንነት ለማስተማር ምቹ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ማዘጋጀት
- ተማሪዎች በተረዱት ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ስጣቸው/ጪቸው፡፡

## 6. የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

- የእኩልነትን ምንነት በመግለፅ ጀምር/ሪ፡፡
- የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎች ግለፅ/ጭ፡፡

### ለ. አቀራረብ

- ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን የእኩልነት መብት ለተማሪዎች በመግለፅ ትምህርቱን መጀመር ትችላለህ/ያለሽ፡፡
- ተማሪዎች ስለ እኩልነት ምንነት ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ መፍቀድ፡፡
- በትምህርት ቤት ውስጥና በህብረተሰቡ ዘንድ ተማሪዎች ያላቸው የእኩልነት መብት የስርዓት

ያታ፣ የሐይማኖት፣ የቋንቋና የባህልን የሚያካትት ነው፡፡

## ሐ.ማጠናከሪያ

- የትምህርቱን ዋና ዋና ሀሳብ በአጭሩ መድገም

## መ. ምዘናና ክትትል

- ተማሪዎች ትምህርቱን መገንዘባቸውን አረጋግጥ/ጭ፡፡

  ይህ የሚሆነው
  - የቃል ጥያቄ
  - ጥያቄና መልስ
  - በቡድን ተቀናጅተው እንዲወያዩ በማበረታታት ነው፡፡

## ክትትል

- በትምህርት ቤት ውስጥና በህብረተሰቡ ውስጥ ተማሪዎች ስላላቸው የእኩልነት መብት በአጭሩ መወያየት፡፡
- በትምህርት ቤት ውስጥና በህብረተሰቡ ውስጥ ተማሪዎች ስላላቸው የእኩልነት መብት ተማሪዎች የሚያቀርቡትን ፅብረቃ መመዘን፡፡

## 3. 3. የእኩልነት አስፈላጊነት

የተመደበለት ክ/ጊዜ 5

1. ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤

   - እኩልነት ለምን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፡፡

2. የትምህርቱ ይዘት

   - የእኩልነት አስፈላጊነት

3. **አጭር አጠቃላይ መግለጫ**

   - ተማሪዎች የእኩልነት አስፈላጊነትን በተመለከተ ሀሳብ እንዲሰጡ ማበረታታት፡፡

4. **የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

   - ህፃናት በትምህርት ቤትም ሆነ በቤት ውስጥ እኩል ሲስተናገዱ/ሲታዩ የሚያሳይ ሥዕል
   - እኩልነትን የሚያሳዩ ፎቶዎችን መጠቀም

5. **የመማር ማስተማር ዘዴ**

   - የግንዛቤ ጥያቄዎች
   - ገለፃ
   - ጥያቄና መልስ
   - የቡድን ውይይት

6. **የማስተማር ሂደት**

ቅድመ ዝግጅት

- አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት መሳሪያዎችና ሰዎች አድልዎ ሲያደርጉ የሚያሳዩ ሥዕሎችና ፎቶዎች
- ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያስታውሱ ማድረግ

## የትምህርቱ አቀራረብ

ሀ. መግቢያ

- መምህር/ት ተማሪዎች የእኩልነት አለመኖር የሚስከትለውን ጉዳት እንዲያነሱ በማድረግ ትምህርቱን ያስተዋውቁ፡፡
- የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ማስተዋወቅ
- ተማሪዎች የእኩልነት አለመኖር የሚያስከትለውን ጉዳት እንዲያነቡና እንዲያስቡ በቂ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ሀሳብ ለመሰንዘር የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን ያንሱ፡፡ ለምሳሌ፡ የእኩልነት አለመኖር ጉዳት አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ. አቀራረብ

ይህ ትምህርት የእኩልነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ጉዳት በአጭሩ በመግለፅ መጀመር ይቻላል፡፡

ሐ. ማጠናከርያ

የትምህርቱን ዋና ሀሳብ በአጭሩ መድገም

መ. ምዘናና ክትትል

1. ምዘና
    - ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መገንዘባቸውን አረጋግጡ፡፡
    - በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩ ማበረታታት
2. ክትትል

- ተማሪዎች ትምህርቱን መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ የግል ወይም የቡድን ስራ መስጠት ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎች በቡድን ሥራ  መሳተፋቸውን አረጋግጡ፡፡
- በእኩልነት ባለመኖር ስለሚመጡ ጉዳቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ሀሳብ መመዘን

የምዕራፍ ሦስት ተግባራት መልሶች

ተግባር 3.1

1. ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ካላቸው የእኩልነት መብቶች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-
    - ጥያቄ የመጠየቅ መብት፤
    - መልስ የማግኘት መብት፤
    - በተጓዳኝ ትምህርት ውስጥ የመሳተፍ መብት፤
    - በሚመለከታቸው ጉዳይ ላይ የመሳተፍ መብት፤
    - የትምህርት ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ የመጠቀም መብትና የመሳሰሉት
2. ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ መወጣት ከሚገባቸው ግዴታዎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- የትምህርት ቤቱን ህግና መመሪያ ማክበር፤
- ለሌሎች ተማሪዎች አርዓያ መሆን፤
- የክፍልና የቤት ስራዎችን በሰዓቱ መስራት፤
- መምህራንን ማክበር
- የትምህርት ቤቱን ንብረት መንከባከብ

ተግባር 3.2

1. ሴቶች ወንዶች የሚሰሩትን ስራ መስራት እንዲችሉ እንዲሁም ወንዶችና ሴቶች እርስ በእርስ በመረዳዳት እኩል መስራት እንዲችሉ
2. መላላክ ፣ውሃ መቅዳት፣ ልብስ ማጠብ ፣ቤት ማጽዳት፣ እንጨት መልቀም፣ ከብት ማገድ

ተግበር 3.3

1. ሁሉም ቋንቋዎች እኩል ደረጃ አላቸው፡፡ ይህም አገልግሎት በመስጠት ሁሉም እኩል ናቸው፡፡ ተናጋሪዎቻቸውን እንደ መግባቢያ መሳሪያ ያገለግላሉ፡፡
2. ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ብዙ ቋንቋዎች ሊነገሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡ አፋን ኦሮሞ፣ አፋን አማራ፣ ሶማልኛ፣ ሀረሪና የመሳሰሉት

ተግባር 3.4

1. የሐይማኖት እኩልነትን ማክበር ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል እንደ ሰላምና መረጋጋት ያለው ህብረተሰብ መፍጠር፣ መቻቻል፣ መዋደድና መደናነቅ

2. ሐይማኖታቸውን አለመናቅና በዓላቸውን አብሮ በማክበር
3. ሰላምና መረጋጋት ማጣት ፣መከባበር

   አለመኖር፣የመናናቅና የመሳሰሉት

ተግባር 3.5

የባህል መገለጫዎች እንደ ቋንቋ፣ሐይማኖት፣ የአለባበስ ሁኔታ፣ባህላዊ ምግብ ፣ ሐዘንና ደስታ የሚገለፅበት መንገድ

ተግባር 3.6

በትምህርት ቤት ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸው የእኩልነት ዓይነቶች መልካም አመለካከትና እኩል እድል የተሰኙት ይገኛሉ፡፡ ያለ አንዳች አድልዎ ተማሪዎች በትምህርታቸው ይመዘናሉ የሚሉትን ማንሳት ይቻላል፡፡

ተግባር 3.7

በእኩልነት አለመኖር ምክንያት የሚከሰቱ ጉዳቶች እንደ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፣አድልዎ፣ አለመስማማት፣ ፀብና ስርዓተ አልበኝነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የምዕራፍ ሶስት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ክፍል አንድ -- እውነት ወይም ሐሰት

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት

## ክፍል ሁለት -- ማዛመድ

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. መ

## ክፍል ሦስት-- ምርጫ

1. ለ
2. ሐ
3. ሀ
4. መ

## ክፍል አራት-- አጭር መልስ

1. ልጆች በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ዘንድ ሊኖሯቸው የሚችሉ ዋና ዋና መብቶች
   - ጥያቄ የመጠየቅ መብት
   - ከአድልዎ የመጠበቅ መብት
   - መልስ የማግኘት መብት
   - በሚመለከታቸው ጉዳይ ውስጥ የመሳተፍ መብት
   - የትምህርት ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ የመጠቀም መብት
2. የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከማክበር ጥቅሞች ውስጥ ሁለቱን ፃፉ፡፡
   - በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የሚፈጠረውን የመማር ብቃት ልዩነት ያጠባል፡፡

- በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለመቀነስና ስራ ለማግኘት
- ሴት ተማሪዎች መብታቸውን እንዲጠቀሙ መርዳት

3. የእኩልነት አለመኖር የሚከተሉትን ጉዳቶች ያስከትላል፡-

የሰብአዊ መብት ጥሰት ፣ግጭት፣ አድልዎ፣ያለመረጋጋት እና ከዚህም በበለጠ በግለሰቦችና ቡድኖች መካከል ጥሩ ያልሆነ ግንኙነትን ይፈጥራል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡ ማሕበራዊ ሕይወት

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ስለ ማህበራዊ ሕይወት ምንነት፣የጥሩ ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያት፣ የማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነትና መልካም ማሕበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ሁኔታዎች ላይ እንዲያተኩሩ ተማሪዎችን ያስታውሳል፡፡

የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች

- የማህበራዊ ሕይወትን ምንነት መግለፅ፤
- የመልካም ማህበራዊ ሕይወት ባህርያትን ማሳየት፤
- የመልካም ማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነትን መግለፅ፤
- ማህበራዊ ህይወት የመፍጠር ጥቅሞችን መለየትና
- ማህበራዊ ህይወትን የሚጎዱ ተግባራትን መግለፅ፡፡

## ትምህርት 4.1 የማህበራዊ ሕይወት ምንነት

የተመደበለት ክ/ጊዜ 5

1. ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤

- የማህበራዊ ሕይወትን ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የመልካም ማህበራዊ ሕይወት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፡፡

2. የትምህርት ይዘት

- የማህበራዊ ሕይወት ምንነት
- የመልካም ማህበራዊ ሕይወት መገለጫዎች

3. **አጭርአጠቃላይመግለጫ**

የሰው ልጅ የጋራ ማህበራዊ ሕይወት አለው፡፡ይህ ማህበራዊ ሕይወት የሰውን ልጅ ከሌሎች ፍጡራን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ማህበራዊ ሕይወት ከሌሎች ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት የመኖር ችሎታ ነው፡፡ ይህም አንድ ሰው ከቤተሰቡ ጋር፣ ካጓደኞቹ ጋር፣ ከመሳሰሉት መልካም ግንኙነት መፍጠርን ያካትታል፡፡ይህ ደግሞ የመልክም ማህበራዊ ሕይወት መገለጫዎች እንደ መከባበር፣ ትዕግስት መኖር፣ አብሮ መጫወት፣ አንዱ ሌላውን መረዳት እና በመሳሰሉት ይገለፃል፡፡

4. **የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

ህፃናት በአንድነት ሲጫወቱ የሚያሳይ ሥዕል ወይም ቤተሰብ በአንድነት ሲወያዩ

የሚያሳይ እና ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፎቶዎች መጠቀም ይቻላል፡፡

5. **የመማር ማስተማር ዘዴ**

የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴች መጠቀም ይቻላል፡፡

- የግንዛቤ ጥያቄዎች
- ተማሪዎችን በትንንሽ ቡድን በመከፈል
- አጭር ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ውይይት

6. **የማስተማር ሂደት**

ቅድመ ዝግጅት

- ስለ መልካም ማህበራዊ ሕይወት ማንበብ
- በተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረበውን ሥዕል መረዳት

- የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት
- ተማሪዎች እንደ መረዳታቸው እንዲመልሱ ማነሳሳት

ሀ. የትምህርቱ መግቢያ

በማህበራዊ ሕይወት ምንነት ላይ በማተኮር በጥሩ ሁኔታ ለተማሪዎች ይግለፁ

- የትምህርቱን ይዘት ለተማሪዎች ይንገሩ፡፡
- ተማሪዎች የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያነሳሱ
- የተማሪዎችን ነገሮችን የመተንተን ችሎታ የሚያበረታቱ ጥያቄዎችን ይጠይቁ ለምሳሌ፡ ማህበራዊ ሕይወት ምንድን ነው?

ለ. የትምህርቱ አካል

የማህበራዊ ሕይወት ምንነትን በምሳሌ ግለፁ፡፡ እንዲለማመዱም አድርጉ፡፡

የተሰጠው ገለፃ ላይ በመመስረት የመልካም ማህበራዊ ሕይወት መገለጫዎችን  ይግለፁ፡፡

ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚታዩትን መልካም ማህበራዊ ሕይወት ከተጨባጭ ምሳሌ ጋር እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡

ሐ. የግንዛቤ ማጠናከርያ

የትምህርቱን ዋና ሀሳብ ማጠቃለል ፡፡ ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ሀሳብ መለየታቸውን  ይጠይቁ፡፡ የትምህርቱን ዋና ሃሳብ በመከለስ ተማሪዎች ያላነሷቸውን ሃሳቦች በመጨመር ትምህርቱን ያጠቃሉ፡፡ የሚከተሉትን ነጥቦች ማንሳት ይችላሉ፡፡

1. አብሮ መኖርንና ማህበራዊ ግንኑነትን እንዴት እንደ ተለማመዱ
2. የመልካም ማህበራዊ ሕይወት መገለጫዎችን በመዘርዘር

## መ. ምዘናና ክትትል

1. ምዘና
    - የተማሪዎችን ግንዛቤ የክፍል ስራና አሳይመንት በመስጠት ይፈትሹ፡፡
    - ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ስለ መልካም ማህበራዊ ሕይወት አኗኗር በምሳሌ እንዲገልፁ ያግርጉ፡፡
2. ክትትል
    - ተማሪዎች በበለጠ የትምህርቱን ይዘት እንዲገነዘቡ አሳይመንት ይስጧቸው፡፡
    - ሁሉም ተማሪዎች ስለ ማህበራዊ ሕይወት ምንነት እንዲረዱ ተሳትፏቸውን ያበረታቱ፡፡
    - ተማሪዎች ከሚሰጡት ግብረ መልስ ስለ ማህበራዊ ህይወት ግንዛቤአቸውን ይመዝኑ፡፡
    - በቡድን የተወያዩትን ለክፍል እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

.

## 4.2 መልካም ማህበራዊ ሕይወት ያለው ሰው ባህሪይ

የተመደበለት ክ/ጊዜ7

### 1. ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤

- መልካም ማህበራዊ ሕይወት ያለው ሰው ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡

### 2. የትምህርቱ ይዘት

የመልካም ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያት

### 3. አጭር አጠቃላይ መግለጫ

የማህበራዊ ሕይወት ምንነትን በተመለከተ ባለፉት የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ተምረዋል፡፡ አሁን ደግሞ  የመልካም ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያትን መዘርዘር ይቀጥላል፡፡ ተማሪዎች በቀላሉ እንዲረዱ እያንዳንዱ ነጥብ በምሳሌ የሚገለፅ ይሆናል፡፡

የትምህርቱን ይዘት በጥልቀት መግለፅ ይጠበቃል፡፡ተማሪዎች ስለ መልካም ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያት እንዲወያዩና  ጥሩ ግንዛቤ እንዲይዙ  መበረታታት አለባቸው፡፡

የመልካም ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያት በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላሉ፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- ከቤተሰብ ( እናት አባት ወንድም እና የመሳሰሉት) ከጓደኛና ጎረቤት ጋር ጠንካራ ግንኙነት መኖር፤
- የግል ሀሳብን በነፃነት መግለፅና የሌሎች ሰዎችንም ሀሳብ ማዳመጥ፤
- የአብሮነትና አብሮ የመስራት ባህሪይ መኖር፤
- ለሰብእና ክብርና ፍቅር መኖር ፣
- ትዕግስት መኖር

- ፀብን ማስወገድ
- የመረዳዳት ባህል መኖር፣ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 4. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- መልካም የቤተሰብ አኗኗርን የሚያሳይ ሥዕል ለተማሪዎች ማሳየት
- የማህበራዊ ሕይወትን የሚያሳይ ሥዕል ለተማሪዎች ማሳየት

## 5. የመማር ማስተማር ዘዴ

የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- የግንዛቤ ጥያቄዎች በመጠየቅ፡፡
- ተማሪዎችን አራት አባላት ባለው ቡድን በመክፈል የመልካም ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያት ላይ እንዲነጋገሩ ማድረግ፡፡
- አጭር ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ውይይት

## 6. የማስተማር ሂደት

ቅድመ ዝግጅት

ተማሪዎች የግል ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

ሀ. የትምህርቱ መግቢያ

ይህን ትምህርት ስለ ማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነት በመግለፅ መጀመር ይችላሉ፡፡

- የትምህርቱን ይዘት ለተማሪዎች ይግለፁ፡፡

- ለተማሪዎች በቂ ጊዜ በመስጠት ስለ ማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነት እንዲያስቡ ያድርጉ፡፡
- ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡
- እንደ ማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነትን ዘርዝሩ የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

ለ. የትምህርቱ አካል

- መምህር/ት የማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነትን በመግለፅ ይጅምሩ፡፡
- እያንዳንዱን ማህበራዊ ሕይወት ያለውን አስፈላጊነት ተማሪዎች በቀላሉ እንዲረዱ በምሳሌ መገለፅ አለበት፡፡
- ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ መበረታታት አለባቸው፡፡

ሐ. የግንዛቤ ማጠናከርያ

የማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነትን በአጭሩ በመግለፅ ትምህርቱን ማጠናከር ይችላሉ፡፡

መ. ምዘናና ክትትል

**ምዘና**

ተማሪዎች ትምህርቱን መረዳታቸውን የክፍል ስራና አሳይመንት በመስጠት መፈተሽ፡፡

ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ስለ ማሕበራዊ ሕይወት አስፈላጊነት ከራሳቸው አኗኗር ዘይቤ ጋር በማያያዝ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡

ክትትል

- ተማሪዎች በበለጠ ትምህርቱን እንዲገነዘቡ በሚገባ ማስተማርና አሳይመንት መስጠት ነው፡፡
- የተማሪዎችን ተሳትፎ ማበረታታት፡፡
- ተማሪዎች የማህበራዊ ሕይወት አስፈላጊነትን አስመልክቶ የሚሰጡትን ግብረ መልስ መመዘን፡፡
- በቡድን የተወያዩበትን ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ ፡፡

# ትምህርት 4.4 የማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮች

የተመደበለት ክ/ጊዜ 4

1. ተማሪዎች ቢያንስ እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፤
   - የማህራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮችን ይዘረዝራሉ
2. **የትምህርቱ ይዘት**

   የማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ሁኔታዎች/ተግባራት
3. **አጭር አጠቃላይ መግለጫ**

ይህ ትምህርት መልካም ማህበራዊ ሕይወትን መጉዳት የሚችሉ ነገሮች ላይ ያተኩራል፡፡ስለዚህ ለተማሪዎች በማህበራዊ ሕይወት ላይ ጉዳት ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮችን በመዘርዘር ገለፃ መድረግ፡፡እነርሱም እንደ አድልዎ ማድረግና ጥላቻን ማሳየት ፣ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት ያለመኖር፣እናትና አባት እንዲሁም ታላላቆችን አለማክበር፣ግልፅነት ያለመኖር የጋብቻ መፍረስና የቤተሰብ መበተን ፣ስራ አጥነት መብዛት ፣መተማመን አለመኖር ፣አንዱ ሌላውን ያለመረዳትና ያለመከባበር ፣ በችግር ጊዜ ያለመረዳዳት ፣የቋንቋ የሐይማኖትና የማንነት ልዩነቶችን ያለመቀበልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህ የማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮች ከጊዜ በሁዋላ የጤና ችግር ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ስለዚህ መልካም ማህበራዊ ሕይወትን ከሚጎዱ ነገሮች እራስን መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡

4. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

አንበሳና አይጥ በሚለው ተረት ውስጥ ቀድሞ የነበራቸው ግንኙነት እንዴት እንደተጎዳና በኋላም እንዴት እንደታደሰ በተጨማሪም ያስገኘውን ውጤት ይግለፁ፡፡

ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸውን በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮችን እንዲያሳዩ ማድረግ ፡፡

5. የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፡፡
- ተማሪዎችን አራት አባላት ባለው ቡድን በመክፈል የመልካም ማህበራዊ ሕይወትን በሚጎዱ ነገሮች ላይ በመወያየትና በተግባር እንዲያሳዩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- አጭር ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ውይይት

6. የመማር ሂደቶች
ቅድመ ዝግጅት

ተማሪዎች የግል ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት

የትምህርቱ አቀራረብ

ሀ. የትምህርቱ መግቢያ

በማህበራዊ ሕይወት ላይ ጉዳት ስለሚያስከትሉ ነገሮች በመግለፅ መጀመር ይችላሉ፡፡

- የትምህርቱን ይዘት ለተማሪዎች ይግለፁ፡፡
- ለተማሪዎች በቂ ጊዜ በመስጠት የማህበራዊ ሕይወትን ስለሚጎዱ ነገሮች ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጉ ፡፡
- ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

- እንደ ማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮችን ዘርዝሩ የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

ለ. የትምህርቱ አቀራረብ

- መምህር/ት ማህበራዊ ሕይወትን ስለሚጎዱ ነገሮች በመግለፅ ይጀምሩ፡፡
- ማህበራዊ ሕይወትን ስለሚጎዱ ነገሮች ተማሪዎች በቀላሉ እንዲረዱ በምሳሌ መገለፅ አለበት፡፡
- ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ መበረታታት አለባቸው፡፡

ሐ. የግንዛቤ ማጠናከሪያ

ማህበራዊ ህይወትን የሚጎዱ ነገሮችን በመዘርዘር ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

መ. ምዘናና ክትትል

ምዘና

- ተማሪዎች በበለጠ ትምህርቱን እንዲገነዘቡ በሚገባ ማስተማርና አሳይመንት መስጠት ነው፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ማሕበራዊ ሕይወትን ስለ ሚጎዱ ነገሮች ተጨባጭ ምሳሌ በመውሰድ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡

ክትትል

- ተማሪዎች በበለጠ ትምህርቱን እንዲገነዘቡ በሚገባ ማስተማርና አሳይመንት መስጠት ነው፡፡
- የተማሪዎችን የማህበራዊ ሕይወትን ስለሚጎዱ ነገሮች እንደ አገኙት ግንዛቤ እንዲሳተፉ ማበረታታት፡፡
- ተማሪዎች ማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮችን አስመልክቶ የሚሰጡትን ግብረ መልስ መመዘን፡፡
- በቡድን የተወያዩበትን ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ ፡፡

## የምዕራፍ አራት ክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

I. ትክክለኛውን ሀሳብ የያዘውን ዓረፍተ ነገር እውነት ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት

II. ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ

1. ሀ
2. መ
3. ሐ
4. መ

III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ

1. የማህበራዊ ሕይወትን አስፈላጊነት ግለፅ/ጭ

   የመዋደድ ስሜትን ለማሳደግ፣ በሀዘንና በደስታ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመካፈል፣ ንቁ አእምሮ እንዲኖረን፣ የተረጋጋ ልብ እንዲኖረን ያደርጋል፣ረጅም እድሜ እንድንኖር ያደርጋል ፣በችግር ጊዜ እንድንረዳዳና አብረን እንድንቆም ያደረጋል ፣ የመዋደድና የመበረታታት ስሜትን ያዳብራል ፣ ሰዎች በፍቅርና በመከባበር አብረው እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡

2. መልካም ማህበራዊ ህይወት ያለው ሰው ባህሪያት ዘርዝር/ሪ

ከቤተሰብና ከጓደኛ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ማድረግ ፣የግል ሀሳብን በግልፅና በነፃነት መግለፀ እና የሌሎች ሰዎችንም መውሰድ፣ለሰዎች ክብር እና ፍቅር መኖር ፣ትዕግስት መኖር፣ ግጭትን ማስቀረት፣ የመረዳዳትና የመጠያየቅ ባህልን ማጎልበት እና የመሳሳሉት ናቸው

.3. ማህበራዊ ሕይወትን የሚጎዱ ነገሮችን ዘርዝሩ

መከፋፈል እና ጥላቻ ማሳየት ፣በቤተሰብና በልጆች መካከል ጥሩ ያልሆነ ግንኙነት መኖር ፣. ህፃናትን በማሳደግ ወቅት መጥፎ ባህሪያትን ማስተማር ፣ ግልፅነት አለመኖር ፣ የጋብቻ መፍረስና የቤተሰብ መበተን ፣ስራ አጥነት መብዛት ፣ጥላቻና መጎዳዳት መብዛት ፣ ወንጀል መብዛት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

# ምዕራፍ 5፡መተጋገዝ እና አብሮ መስራት

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 21**

## መግቢያ

ውድ መምህር/ት፣-ይህ ምዕራፍ በጋራ መረዳዳት እና በቡድን መስራት ላይ ያተኩራል። በተለይም፣ በህብረተሰብ ውስጥ የመረዳዳት ባህሎችን ምሳሌ እንደ፡ደቦ ወይም ጂጊ፣ እድር እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ በቡድን ስራ የመረዳዳት ባህል ናቸው። በተጨማሪም፣ የቡድን እና የጋራ ትብብር ስራ መርሆዎችን ይዘረዝራል፡፡ እንዲሁም ግብረመልስ ለመስጠት እና ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን፣ በተግባቦት ሥራ፣ በክርክር እና የጊዜ አጠቃቀም እና አስተዳደር ላይ ያተኩራል።

## ምዕራፍ 5፡1 መተጋገዝ እና አብሮ መስራት

የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 21

### የምዕራፉ ትምህርት ውጤቶች፡-

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፤

- የመረዳዳት ሥራ መቼ መቼ እንደሚያስፈልግ መግለጽ፣
- የቡድን ስራ ለምን ጥቅም ላይ እንደሚውል ማስረዳት፣
- በአካባቢያቸው የሚገኙትን የመረዳዳት ባህል ሥራን መግለጽ እና
- በጋራ መረዳዳት እና በቡድን ስራ መሳተፍ፣ መነሳሳት።

### ትምህርት 5.1፡የጋራ መረዳዳት እና የቡድን ስራ፤

(የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 9)

### 1. ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤

- በጋራ መረዳዳት ለምን እንደሚያስፈልግ ማስረዳት፣

- በቡድን ስራ ውስጥ በንቃት መሳተፍ፣

2. **ይዘቶች**

   1. የጋራ የመረዳዳት እና የቡድን ስራ፣

      • በህብረተሰብ ውስጥ የትብብርእና የቡድን ስራ ባህል፡- እንደ ደቦ/ጂጊ እና እድር እና በትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ የቡድን ስራ፤

3. **አጠቃላይ አጭር መግለጫ**

ውድ መምህር/ት፣-የትብብር እና የቡድን ስራ ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አንድ ላይ ሆነው አንድ ግብ ላይ ለመድረስ አብረው የሚሰሩ ናቸው። የቡድን ስራ እና ትብብር በአንድ ሰው ለማከናወን አስቸጋሪ የሆኑትን ስራዎች ለማቃለል እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ይረዳሉ፡፡ እነርሱም እነ ደቦ እና እድር ናቸው፡፡

4. **የምትጠቀሙት የመማሪያ ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች**

   - በማህበረሰቡ እና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰሩ ቡድኖች ስዕል (ምስል 5.1-5.3)።

5. **የማስተማር ስልቶች**

   - በክብ ቅርጽ ቡድኖችን በመመስረት እና ተማሪዎች በትብብር እና በቡድን ስራ ትርጉም ላይ እንዲሰሩ ማድረግ።
   - ተማሪዎችን በማኅበረሰባቸው እና በት/ቤታቸው ውስጥ በሚገኙ የትብብር እና የቡድን ስራ ውስጥ ማሳተፍ እና እንዲወያዩ ማድረግ።

6. **የመማር እና የማስተማር ሂደት፤**

**ቅድመ-ትምህርት ዝግጅት**

- የጋራ መረዳዳትን እና የቡድን ስራን መግለጫን ያንብቡ።
- በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች አስረዱ፡፡

**የመማሪያ መግቢያ**

- የትብብር ትምህርት እና የቡድን ስራን ያስተዋውቃሉ።
- የትምህርቱን ዓላማ እንዲያብራሩ ያድርጉ።
- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሀሳቦችን ውስጥ የተማሪዎችን አእምሮ የሚያነቃቁ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

**የትምህርቱአካልአቀራረብ**

- ስለ ትብብር እና የቡድን ስራ መግለጫ ይስጡ።
- በቡድን፣ ማህበረሰቦች እና ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የስራ ዓይነቶችን ለተማሪዎች ይግለጹ።

**ግንዛቤን ማጠናከር**

- የትብብርን እና የቡድን ስራ ቁልፍ ነጥቦችን፣ እንደገና እንዲረዱትመስራት።
- የትብብር ጽንሰ-ሐሳቦችን እንዲረዱ እና እንዲገነዘቡ እርዷቸው።

**ግምገማ እና ክትትል**

- ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድኖች ማደራጀት እና የቡድን ስራ እንዲሰሩ እርዷቸው።

# 5.2፥በማህበረሰብ እና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትብብር እና የቡድን ስራ ባህል

(የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 12)

1. **ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤**
   - በማህበረሰባቸው እና በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ያሉትን ባህላዊ የድጋፍ ቡድኖችን ይዘርዝራሉ።
   - በማህበረሰባቸው እና በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ያሉትን የቡድኖች ስራ ጥቅሞች ዘርዝረው ይገልጻሉ።
2. **ይዘቶች**
   - የጋራ መረዳዳት በማህበረሰብ ውስጥ፤
   - የቡድን ስራ በትምህርት ቤት ውስጥ፤
3. **የአጠቃላይ አጭር መግለጫ**

በኦሮሞ ህዝብና በሌሎች ብሄረሰቦች መካከል የመተባበር ባህል አለ። በብረተሰቡ ውስጥ የትብብር ስራ ባህላዊ ቴክኒኮች እንደ ደቦ እና እድር እና በት/ቤት ውስጥ የቡድን ጥናት ሥራ እና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ቡድኖች መከተል ያለባቸው የተለያዩ መርሆዎች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ሁሉም የቡድን አባላት ብቻውን ሳይሆን አብሮ መስራት የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ ማመን አለባቸው።

4. **የትምህርት መማሪያ ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች**
   - በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የጋራ መረዳዳት እና የቡድን ስራ ችሎታ ምስሎች፤

## 5. የማስተማር- መማር ዘዴዎች

- ተማሪዎችን በትብብር እና በቡድን የመስራት ችሎታን በአቋራጭ አቀራረብ መወያየት ላይ ያሳትፉ።
- ተማሪዎች ከትምህርት ቤታቸው እና ከማህበረሰቡ የትብብር ተግባራትን እና የቡድን ስራን አስመስለው እንዲሰሩ ማበረታታት።
- ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ በማድረግ፣ የጋራ መረዳዳት እና የቡድን ስራ አስፈላጊነት ላይ አወያዩዋቸው።

## 6. የመማር እና ማስተማር ሂደት

### የቅድመ ትምህርት ዝግጅት

- በመግለጫዎች፣ መመሪያዎች፣ ችሎታዎች እና መስፈርቶች ላይ ተጨማሪ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ፤

## 7. የትምህርት አቅርቦቶች

- የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት።
- በመማሪያ መጽሀፉ ላይ የሚታዩትን የስዕሎች መልእክት ይረዱ፡፡

### ሀ) የትምህርቱ መግቢያ

- ተማሪዎች የትምህርቱን ዓላማ ማወቅ አለባቸው።
- ከመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ሀሳቦችን የሚያጎሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

### ለ) የትምህርቱ አካል አቀራረብ

በእነዚህ ይዘቶች ስር፣ በመማሪያመጽሀፍ ውስጥ ያለውን ምስል ያሳዩ፤

### ሐ) ግንዛቤን ማጠናከር

- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በተሰጡት ይዘቶች ላይ ያተኮሩ ዋና ዋና ነጥቦችን ይከልሱ፤

## መ) ግምገማ እና ክትትል

የጋራ መረዳዳትን እና የቡድን ስራን እንዲገልጹ ተማሪዎችን ጠይቋቸው፡፡

ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድኖች አደራጅተው እና በዚህ ትምህርት ስር ባለው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉትን ተግባራትን እንዲሰሩ እርዷቸው።

## 5.3፡መተጋገዝ እና አብሮ የመስራት መርሆዎች፤

1. **ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤**
   - በትብብር ሥራ ውስጥ የሚሰሩ አባላት ሊኖራቸው የሚገባቸውን ባህሪያት ይዘርዝራሉ።
2. **ይዘቶች**
   - የመተጋገዝ እና አብሮ የመስራት ባህሪያት ወይም መርሆዎች፤
3. **የአጠቃላይ አጭርመግለጫ**

   ከአንዳንድ የጋራ መተጋገዝ እና አብሮ መስራትመርሆዎች ውስጥ፤
   - ጥሩ ግንኙነት፣
   - የግል ኃላፊነት፣
   - የተግባቦት (ግንኙነት) ችሎታዎች፣
   - ግንኙነቶችን (መቀራረብን) ማጠናከር፤
4. **የመማሪያ ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች**
   - ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲወያዩ በማድረግ የተማሪን ግንዛቤ ማጠናከር።
5. **የመማር እና የማስተማር ዘዴዎች**

ውድ መምህር/ት፣ ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች በጋራ ዕርዳታ እና የቡድን የስራ መግለጫዎች ላይ እንዲወያዩ እና የቡድን ስራ እንዲሰሩ ያድርጉ። እያንዳንዱ ተማሪ ችሎታቸውን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ጠይቋቸው፣ ሀሳባቸውን በግልፅ መግለጽ መቻላቸውን ወይም አለመቻላቸውን ያረጋግጡ።

6. **የቅድመ ትምህርት ቤት ዝግጅት**
   - የቡድኖች አባላትን ገለጻ፣ መርሆዎች እና ክህሎቶች እና የመተጋገዝ እና አብሮ መስራት አስፈላጊነት ላይ ተጨማሪ ቁሳቁሶችን ያንብቡ።

## 7. የትምህርት አቅርቦቶች

- የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት።

### ሀ) የትምህርቱ መግቢያ

- ስለመርሆች፣መተጋገዝ እና አብሮ መስራት ስራ ማሳወቅ።
- ከመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ሀሳቦችን የሚያጎሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
- ተማሪዎችን ስለትምህርቱ፣ እንደ መመሪያ፣ መተጋገዝ እና አብሮ መስራት፣ ወዘተ የመሳሰሉትን በቃል ይጠይቁ።

### ለ) የትምህርቱ አካል አቀራረብ

መርሆዎችን፣ የጋራ መረዳዳትን እና የቡድን ስራን ይግለጹ።

### ሐ) ግንዛቤን ማጠናከር

- የመተጋገዝ እና አብሮ መስራትመርሆዎችን ዝርዝር እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።

### መ) ግምገማ እና ክትትል

ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድኖች አደራጅ እና በዚህ ትምህርት ስር ባለው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉትን ተግባሮችን እንዲሰሩ እርዷቸው ።

እነዚህን የመተጋገዝ እና አብሮ መስራት መርሆዎች በኑሮአቸው ውስጥ እና በቡድን ስራ ሲሳተፉ እንዴት ጥሩ እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያዩ እርዷቸው።

## 5.4፡መተጋገዝ እና አብሮ የመስራት ባህል፤

1. **ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤**
    - በመተጋገዝ ባህል ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ባህሪያት ይዘረዝራሉ።
2. **ይዘቶች**

    ሀ) አስተያየት ወይም ግብረ መልስ ለመስጠት እና ለመቀበል ዝግጁመሆን፣

    ለ) የተግባቦት ሥራ

    ሐ) ክርክር

    መ) ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
3. **የአጠቃላይ አጭር መግለጫ**

የመተጋገዝ እና አብሮ መስራት ባህል ግብረመልስ ለመስጠት እና ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ ቁልፍ የሆኑ ነጥቦችን፣ ተግባቦትን፣ ክርክርን እና የጊዜ አጠቃቀምን ያካትታል።

የሌሎች ሰዎችን መረጃ ወይም ሀሳብ ለማዳመጥ ፈቃደኛ መሆን እና ግብረመልስ ለመስጠት ዝግጁ መሆን ማለት ነው። ይህ በቡድኑ ውስጥ ያሉ የተቃዋሚዎቻችንን አስተያየት ማዳመጥን ይጨምራል። በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ ሌሎችን ማሳመን ብልህነት ነው። በእውነታዎች ላይ በመመስረት መስራት የቡድን አባላት ግንኙነቶችን ያጠናክራል.

ክርክር በአንድ ስብሰባ ውስጥ የአንድ የተወሰነ ጉዳይ መደበኛ ውይይት ነው። ተከራካሪዎች በተመልካቾች ስሜት ላይ ተመሥርተው በጉዳዩ ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር የሚሞክሩበት ዘዴ ነው።

የጊዜ አስተዳደር ማለት ሥራን በማደራጀት እና በማቀድ ሂደት ውስጥ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች መካከል ጊዜን እንዴት እንደሚከፋፍሉ ያሳያል። ይህ ከየትኞቹ ስራዎች ውስጥ ቅድሚያ እንዲሰጡ ይረዳል፡፡.

**4. የመማር እና የማስተማር ዘዴዎች**

**የቡድንውይይት**

**ክርክር**

**ተግባቦት**

**ለምዕራፍ 5 ተግባር የተሰጡ መልሶች**

**ተግባር 5.1**

1. መተጋገዝ እና አብሮ መስራት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎችን ያካትታል፡፡

2. በተናጥል ሳይሆን በቡድን ውስጥ መሥራት የተሻለ እንደሆነ ይጠቁሙ፡፡

ስለዚህ፣ ተማሪዎች በቡድን መስራት ስለሚያስገኛቸው ጥቅሞች እንዲነግሩዎት ይጠበቅባቸዋል፣ እነዚህም አዳዲስ ሀሳቦችን ማካፈል፣ አንዳንድ ከባድ ስራዎችን ቀላል ማድረግ እና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል። ተማሪዎች በጋራ የመስራትን ጥቅሞች በተናጠል ከመስራት ጋር እንዲያወዳድሩ ያድርጉ።

**ተግባር 5.2**

1. በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን በመምከር፣ በመባረክ እና በማስታረቅ ይታወቃል።

2. ደቦ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለአንድ ሰው ወይም ለጥቂት ሰዎች አስቸጋሪ የሆኑ ተግባራትን በአንድነት በመሰባሰብ በቀላሉ ለማጠናቀቅ ያስችላል።

3. ከዚህ ታሪክ የተማርኩት የቡድን ስራ ጥቅሞች በጣም ከፍተኛ ናውን ነው።

4. የተለያየ መልስ መስጠት ስለሚችሉ መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው።

**ተግባር 5.3**

1. የጨሊያ መንደርን እድር በመንደሩ ማህበረሰብ ዘንድ እርስ በርስ መረዳዳት፣ መደጋገፍ፣ ወዘተ.
2. ተማሪዎች መንደራቸው ውስጥ ያሉትን የዕድር ስሞች እንድናገሩ አበረታቷቸው።

**ተግባር 5.4**

1. የቡድን ስራ በትምህርት ቤት ላሉ ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ተማሪዎች
   እውቀታቸውን፣ ችሎታቸውን እና ልምዶቻቸውን እንዲያካፍሉ ይረዳቸዋል።
2. የለሊስቱ ትምህርት ቤት የተሸለመው ተማሪዎቹ በቡድን በመስራት ባህል
   ከፍተኛ ውጤት በማምጣታቸው ነው።

**ተግባር 5.5**

1.መልካም ግንኙነት፣ የግለሰብ ኃላፊነት፣የቡድን ስራ፣ እና ግንኙነቶችን ማጠናከር፡

2. የተማሪዎችን የተላያዩ መልሶች ይቀበሉአቸው።

**ተግባር 5.6**

1. የሌሎችን አስተያየት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን፣ የሌሎችን አስተያየት ለመቀበል ምን ያህል ፈቃደኛ እንደሆኑ ያሳያል።
2. የሌሎችን አስተያየት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ብቻውን በቂ አይደለም።
   የራሳቸውንም ሃሳብ ግልጽነት እንዲያሳድጉ ምራቸው፡፡

**ተግባር 5.7**

እባክዎ መምህር ተማሪዎች አንድን ርዕስ እንዲመርጡ እና ከመምህራቸው ጋር እንዲከራከሩ አበረታታቸው።

**ተግባር 5.8**

1. መረጃን ለመስጠት፣ ለመቀበል እና ለመለዋወጥ መግባባት አስፈላጊ ነው። እርስ በርስ ለመደማመጥ፣ በግልፅ ለመነጋገር እና የተሳታፊዎችን የተለያዩ አመለካከቶች ለማክበር ይረዳል።

2. የሐሳብ ልውውጥ በትኩረት ማዳመጥን፣ ግልጽ የሆነ ግንኙነትን እና የተሳታፊዎችን የተለያዩ አመለካከቶች ማክበርን ይጠይቃል።

**ተግባር 5.9**

1. ማርታ በትምህርትዋ ጎበዝ ተማሪ ናት።
2. ቤተሰቦቿም በትኩረት ይከታተሏታል።
3. የራሳቸውን ሀሳብ ሳይፈሩ እንድያቀርቡ አግዛቸው።

# በምዕራፍ ውስጥ ለጥያቄዎች መልሶች

## ክፍል አንድ፡ እውነት/የውሸት ጥያቄዎች

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. ውሸት
5. እውነት

## ክፍል II፡ ተዛማጅ ጥያቄዎች

1. ለ  2. ሐ  3. መ  4. ሀ

**ክፍል III: አማራጭ ጥያቄዎች**

1. ለ 2. ለ

**ክፍል IV አጭር መልስ ነጥቦች**

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች እንዴት እርስ በርስ እንደሚደጋገፉ

   ቤተሰቦቻቸውን እንዲጠይቁ እና ግንዛቤ ካገኙ በኋላ ለክፍላቸው ይንገሩ።

2. ተማሪ ክርክር ሲያካሂድ ከቤተሰብ፣ ከጎረቤትና ከሽማግሌዎች ልምድ መውሰድ

   አለበት።

# ምዕራፍ 6፡ባህል

(የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 20)

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ስለ ባህል ብዝሃነት ያስተምራል። የባህል ብዝሃነት አስፈላጊነት ግንዛቤን ይፈጥራል። የሀገራችን ህዝቦች የራሳቸው ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ታሪክ፣ አለባበስ፣ የስራባህል፣ ባህላዊ ምግብ እና የጋብቻ ባህል እንዳላቸው ያስታውሰናል። በመጨረሻም፣ ተማሪዎች የባህልብዝሃነትን ማስተናገድ ያለውን ጠቀሜታ እና እሱን ማስተናገድ የሚቻልባቸውን መንገዶች ያስተምራል።

### የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች፡

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ፣ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ።

- ባህልብዝሃነትይገልጻሉ፤
- የባህልብዝሃነትን አስፈላጊነትያብራራሉ፤
- የህብረተሰቡን የባህል ስብጥር ያደንቃሉ፤
- ባህላዊ የመስተንግዶ መንገዶችን ይለያሉ፡፡

## 6.1፡መድብለ ባህላዊነት

1. **ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤**
   - የባህል ብዝሃነትንይገልጻሉ።
2. **ይዘት**
   - የባህል ብዝሃነትምንነት
3. **አጠቃላይ አጭር መግለጫ**

   የመድብለ ባሕላዊነት የተፈጠረው በቋንቋ፣ በባሕል፣ በታሪክ፣ በሃይማኖትና በጾታ፣ በማኅበራዊ ደረጃ ልዩነት ነው።
4. **የመማሪያ ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች**
   - የህዝቡን የባህል ብዝሃነትን የሚያሳዩ ምስሎች፣
   - የአካባቢዎን ሰዎች ባህል በማስጎብኘት።
5. **የማስተማር ዘዴዎች**

   ተማሪዎች በቡድን ውስጥ ስላለው የብዝሃነት ትርጉም እንዲወያዩ ያድርጉ። ለምሳሌ ጥያቄ በመጠየቅ፣ በቡድን ውይይት፣ ወዘተ
6. **የመማር እና የማስተማር ሂደት**

   **ለትምህርት አሰጣጥ ቅድመ ዝግጅት**

   ተስማሚ የትምህርት ድጋፍ ሰጪ እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡፡ በዚህ ትምህርት የተነሱትን ዋና ዋና ነጥቦች ለተማሪዎቹ

በማቅረብ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታታት ይችላሉ።

## 7. የትምህርት አቅርቦቶች

### ሀ) የመማሪያ መግቢያ

• አጭር ርዕስ ለተማሪዎች በማቅረብ የብዝሃነትን ትርጉም በማብራራት ላይ ያተኩሩ

• የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ማሳወቅ።

• ተማሪዎች የትምህርቱን መልእክት እንዲረዱ የመረዳት ጥያቄዎችን ያበረታቱ

• አመራማሪ ጥያቄዎችን ማንሳት።

### ለ) የትምህርቱ አካል አቀራረብ

• የባህል ብዝሀነት ትርጉምን በማብራራት ውይይታችሁን ጀምሩ። እንዲሁም እነዚህን

ተግባራዊ ለማድረግ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ላይ ተወያዩ።

• በተሰጡት መግለጫዎች ላይ በመመስረት፣ ልዩነትን ለመረዳት እና ለመተግበር

የሚረዱ ቁልፍ መግለጫዎችን ማሳየት እና ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

• ተማሪዎችቻችሁ በአካባቢያቸው ካሉ የባህል ልዩነቶች የተጨባጭ ህይወት

ምሳሌዎችን እንዲያቀርቡ እርዷቸው።

**ሐ) ግንዛቤን ማጠናከር**

የትምህርቱን ዋና ትርጉሞችን ማጠቃለል፡፡ በተማሪዎች ያልተጠቀሱትን ጨምሮ ሁሉንም አስፈላጊ ነጥቦች በመገምገም ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲለዩ አብራሩ። በመቀጠል ያቀረቡትን ትምህርትዎን ያጠናክሩ።

**መ) ግምገማ እና ክትትል፤**

**ግምገማ፣**

ተማሪዎች ትምህርቱን መረዳታቸውን ያረጋግጡ። ይህ ሊተገበር የሚችለው በሚሰጠው የክፍል ውስጥ ሥራና መልመጃ ሊከናወን ይችላል፡፡ መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የባህል ብዝሃነት ትርጉም እንዲወያዩ እና ብዝሃነትን በመተግበር ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ማበረታታት ይችላል።

**ክትትል፣**

ተማሪዎች ያስተማራችሁትን ትምህርት እንዲገነዘቡ ለመርዳት የቤት ስራን መስጠት ትችላላችሁ። በባህል ብዝሃነት ምንነት ላይ ሀሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ ሁሉንም ተማሪ ባሳተፈ መልኩ ለሁሉም የቡድን አባላት ስጡ።

- የተማሪዎችን የመድብለ ባሕላዊ መግለጫዎች ግንዛቤ ገምግም፣
- ተማሪዎች የቡድናቸውን ግኝቶች ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## 6.2፡የባህል ብዝሀነት መሰረቶች

(የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 5)

### 1. ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤

- የባህል ብዝሀነትን መሰረታዊ ነገሮችይለያሉ፣
- የማህበረሰቡን ባህላዊ ብዝሀነትን ያደንቃሉ፡፡

### 2. ይዘቶች

- የባህል ብዝሀነት መሠረቶች።

### 3. አጠቃላይ አጭር መግለጫ

የባህል ብዝሀነት ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ሊለያዩ እንደሚችሉ ያስተምራል። እነዚህ ልዩነቶች የሚታዩ እና የማይታዩ ናቸው፡፡ እነዚህም ልዩነቶች በግለሰብ እና በቡድን ደረጃ የእርስ በርስ ልዩነቶችን ያካትታሉ፡፡

### 4. የመማሪያ ድጋፍ ቁሳቁሶች

- የህዝቡን ብዝሀነት የሚያሳዩ ምስሎች፤

### 5. የማስተማር ዘዴዎች

የሚከተሉትን ስልቶች በመጠቀም ይህንን ክፍል ይመራሉ፤

ተማሪዎች ስለ ልዩነት አገላለጽ በጥንድ እንዲወያዩ ጠይቋቸውና፤

- ጥያቄዎችንይጠይቁ
- የቡድን ውይይት ያድርጉ፡፡

### 6. የመማር እና የማስተማር ሂደት

የቅድመ ትምህርት አሰጣጥ ዝግጅት፤

ተስማሚ የትምህርት ድጋፍ ቁሳቁሶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡፡ በዚህ ትምህርት የተነሱትን ዋና ዋና ነጥቦች ለተማሪዎቹ

በማቅረብ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታታት ይችላሉ።

## 7. የትምህርት አቅርቦቶች

### ሀ) የትምህርቱ መግቢያ

- በርዕሱ ላይ ለተማሪዎች አጭር ማብራሪያ በማቅረብ የብዝሃነት ጽንሰ-ሀሳብን

በማብራራት ላይ ያተኩሩ፣

- የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ማሳወቅ፣
- ተማሪዎች የትምህርቱን መልእክት እንዲረዱ የመረዳት ጥያቄዎችን በመጠየቅ

ያበረታቱ፣

- የማሰብ ችሎታን የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን ጠይቋቸው።

### ለ) የትምህርቱ አቀራረብ

- የባህል ብዝሀነት ትርጉምን በማብራራት ውይይታችሁን ጀምሩ።እንድሁም እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ በምሳሌዎች ላይ ተወያዩ፤
- በተሰጠው መግለጫ ላይ በመመስረት፣ ልዩነቱን ማብራራት አስፈላጊ ነው፡፡

### ሐ) ግንዛቤን ማጠናከር

የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው። በተማሪዎች ያልተጠቀሱትን ጨምሮ ሁሉንም አስፈላጊ ነጥቦች

በመገምገም የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ተማሪዎች እንዲለዩት ያብራሩ። በመቀጠል ትምህርትዎን ያጠናክሩ።

### መ) ግምገማ እና ክትትል

**ግምገማ፤**

ተማሪዎች ትምህርቱን መረዳታቸውን ያረጋግጡ። ይህ በክፍል በሚሰጠው መልመጃ ወይም የክፍል ውስጥ ስራዎች ሊከናወን ይችላል፡፡ መምህሩ/ርቷ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት  በባህል ብዝሀነት ትርጉም ላይ እንዲወያዩ ማበረታታት አለበት/ባት።

**ክትትል፤**

ተማሪዎች ያስተማራችሁትን ትምህርት መገንዘባቸውን ለመገምገም የቤት ስራን መስጠት ትችላላችሁ።

# 6.3፡የባህል ብዝሀነትን ማስተናገድ አስፈላጊነት

(የተመደበው ክፍል ጊዜ: 4)

## 1. ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤

- ብዝሃነትን ማስተናገድ ያለውን ጠቀሜታ ያብራራሉ።

## 2. ይዘቶች

- የባህል ብዝሀነትን ፍላጎት ማስተናገድ፣

## 3. አጠቃላይ አጭር መግለጫ

ውድ መምህር/ት፣ ብዝሃነትን ማስተናገድ አስፈላጊ የሆነባቸው አንዳንድ ምክንያቶች፡-

- በሰላም እና በስምምነት ለመኖር፣
- የተለያዩ የባህል ቡድኖች ፈጠራን እንድናዳብር እና አዳዲስ አሰራሮችን

  እንድናገኝ ሊረዱን ስለሚመጡና
- የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የቋንቋ ክህሎትን፣ አዲስ የአስተሳሰብ መንገዶችን፣ አዲስ እውቀትን እና የተለያዩ ልምዶችን ያበረክታሉ።

## 4. የመማሪያድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች

- የባህል ብዝሃነትን የሚያሳዩ ሥዕሎች፤

## 5. የማስተማር ዘዴዎች

የታሰቡ የማስተማር ስልቶች፡-

- የመረዳት ጥያቄዎችን ተለማመዱ፤
- የብዝሃነትን አስፈላጊነት በመረዳት ረገድ ክፍተቶች ባሉባቸው ቦታዎች ላይ ተወያዩ፤
- ቃለመጠይቆች አድርጉ፤
- የቡድን ውይይት አድርጉ፤

## 6. የመማር እና የማስተማር ሂደት

**የቅድመ ትምህርት አሰጣጥ ዝግጅት፤**

- ተማሪዎች በብዝሃነት ላይ እንዲያስቡበት ጊዜ አስቀድመው ይስጧቸው፤

## 7. የትምህርቱ አቅርቦቶች፤

### ሀ) የመማሪያ መግቢያ

ተማሪዎች ስለብዝሃነት አስፈላጊነት ሀሳባቸውን እንዲያነሱ በማበረታታት ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ።

- ስለትምህርቱ ዓላማ ተማሪዎችን ያሳውቁ።
- ተማሪዎች ስለብዝሃነት ለማንበብ እና በአስፈላጊነቱ ላይ ለማሰላሰል በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ማመቻቸት።
- ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚገፋፉ ጥያቄዎችን አንሳ።

### ለ) የትምህርቱ አቀራረብ

ለዚህ ትምህርት፣ ተማሪዎችን በመገምገም መጀመር ይሻላል፡፡

እንዲሁም፣ ብዝሃነትን የማስተናገድ አስፈላጊነትን ከተማሪዎች ጋር መወያየቱን ቀጥል።

**ሐ) ግንዛቤን ማጠናከር**

- የትምህርቱን ዋና ፅንሰ ሀሳቦች ማጠቃለል።
- የባህል ብዝሃነትን ፍላጎት ማስተናገድ።

**መ) ግምገማ እና ክትትል፤**

**ግምገማ፣**

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን ያረጋግጡ። ይህን ማድረግ የሚቻለው ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እና ብዝሃነትን ማስተናገድ ስላለው ጠቀሜታ እንዲወያዩ በማበረታታት ነው።

**ክትትል፣**

- ልዩነትን ማስተናገድ አስፈላጊነት ላይ ያላቸውን አመለካከት ይገምግሙ።

## 6.4፡መድብለ ባህላዊነትን ማስተናገድ የሚቻልባቸው መንገዶች

(የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 3)

1. **ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገቡ የመማር ብቃት፤**
    - ተማሪዎች ብዝሃነትን ማስተናገድ የሚቻልባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ።
2. **ይዘቶች**
    - የባህል ብዝሃነትን መንገዶችን ማስተናገድ፣
3. **አጠቃላይአጭርመግለጫ፤**

የሚከተሉት መንገዶች የባህልን ብዝሃነትን ለማስተናገድ የምንጠቀምባቸው ናቸው።

- የብዝሃነት እውቅና፣
- የራስን ባህል ከሌሎች የበላይ ወይም የበታች አድርጎ ከመመልከትመቆጠብ፤
- ልዩነቶችን ማክበር፣
- በግለሰብ ወይም በቡድን ህይወት ላይ እንደ ኋላቀር አድርጎ አለመውሰድ፣
- የብዝሃነት ተቀባይነትን እና አስተዋጽዖን መገንዘብ፣
- የሌሎች ባህሎች ለህብረተሰቡ የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ዋጋ መስጠት፣
- የሌሎች ሰዎችን ባህል ለማድነቅ አእምሮ እንዲኖረን ያስፈልጋል፣
- የባህል ብዝሃነት ቡድኖችን አስተዋፅኦ ማበረታታት እና
- በግልስህተቶች ላይራስንመተቸትእናበልዩነትውስጥያሉትንልዩነቶች በመቻቻል፣ብዝሃነትን እና አንድነትን ማጠናከር። ይህንንም

ለማሳካት ሰዎች እራሳቸውን እና ሌሎችን ማጠናከር እና ማበረታታት አለባቸው፡፡

4. **የመማሪያ ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች**

- በተለያዩ የባህል በዓላት ላይ የተገኙ ብሔር ብሔረሰቦችንሥዕሎች አሳይ።

5. **የመማር እና የማስተማር ዘዴዎች**

እነዚህ የማስተማር ስልቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የመረዳት ጥያቄዎችን ይጠይቁ
- ጥያቄዎች እና መልሶች
- የቡድን ውይይት

6. **የመማር እና የማስተማር ሂደት**

**የቅድመ ትምህርት አሰጣጥ ዝግጅት፤**

- ተማሪዎች ስለ እያንዳንዱ ሀሳብ ግንዛቤያቸውን አስቀድመው እንዲያስቡበት ጊዜ ይስጡ።

7. **የመማሪያ አቅርቦቶች**

**ሀ) የትምህርቱ መግቢያ**

- ተማሪዎች ብዝሃነትን ማስተናገድ የሚችሉባቸውን መንገዶች ልምዳቸውን እንዲወስዱ በማበረታታት ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ።
- ሊያነሷቸው የሚችሉ ጥያቄዎች “ማህበረሰባቸው የባህል ብዝሃነትን እንዴት እንደሚያስተናግዱ  ግለጽ” የሚለውን ሊያካትቱ ይችላሉ።

**ለ) የትህርቱ አቀራረብ**

- ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለመወያየት አንዳንድ ርዕሶችን መስጠት ይችላሉ፡፡
- 

**ሐ) ግንዛቤን ማጠናከር**

- የትምህርቱን ቁልፍ ቃላት ፍቺ ማጠቃለል።
- ልዩነትን ለማስተናገድ መንገዶችን ማጠናከር።

**መ) ግምገማ እና ክትትል**

ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት እና የማህበረሰብ ልዩነትን ማስተናገድ በሚቻልበት መንገድ እንዲወያዩ ማበረታታት ይችላሉ።

ማህበረሰቡ የባህል ልዩነታቸውን እንዴት ማስተናገድ እንደሚችል ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ያድርጉ

## ለምዕራፍ 6 ተግባር የተሰጡ መልሶች

**ተግባር 6.1.**

1. የባህል ብዝሃነት ማለት የተለያዩ ባህሎች ያላቸው ማህበረሰብ አብሮ መኖራቸውን የሚገልጽ ነው።
2. የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በብሄረሰብ በዓላት ቀን የባህል ልብስ በመልበስ ቆንጅተው በመዋላቸው ደስ ብሏቸዋል።
3. በራሳቸው ቋንቋ እና ባህል እንዲኮሩ እና የሌሎችንም ባህል እንዲያደንቁ መንገዱን ከፍቶላቸዋል።

**ተግባር 6.2.**

1. ሐ
2. መ
3. ለ
4. ሀ

**ተግባር 6.3.**

የቡድን ስራ፡ ተማሪዎች የባህል ብዝሃነት ምን ምን እንደሚያካተቱ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ። ከውይይቱ በኋላ ውጤቶቻቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

## በምዕራፍ ውስጥ ለጥያቄዎች መልሶች፤

### ክፍል አንድ እውነት/ሐሰት ጥያቄዎች

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት

### ክፍል ሁለት አዛምድ

1. ሐ
2. ሠ
3. መ
4. ለ
5. ሀ

### ክፍል ሦስት አጭር መግለጫ ስጥ

1. **የባህል ብዝሃነት አስፈላጊነት**
   - ዘላቂ ሰላም እንዲኖር፣
   - የመቻቻል ባህልን ለማጠናከር፣
   - በባህል ብዝሃነታችን ቱሪዝምን ማስተዋወቅ፣
   - የሀገራችንን ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች እና ባህሎች እውቀት ማሳደግ እና
   - ከሁሉም በላይ ብዝሃነት ሀገርን በአንድነት ለመገንባት ትልቅ ሚና ይጫወታል።
2. **የባህል ብዝሃነት ከሚስተናገዱባቸው የተለያዩ መንገዶች መካከል፤**

- የተለያዩ ባህሎችን እውቅና መስጠት፣
- የራስን ባህል የበላይ ወይም የበታች አድርጎ ከመመልከት መቆጠብ፣
- ያሉትን ባህሎች ማክበር፣
- የግል ወይም የቡድን ህይወትን እንደ ኋላቀር አለመመልከት፣
- ባህሎች ለህብረተሰብ እድገት ላደረጉት አስተዋፅዖ እውቅና መስጠት፣
- የሌሎችን ባህል ለማድነቅ መቀበል፣
- ከተለያዩ ቡድኖች የሚደረጉ መዋጮዎችን ማበረታታት፣
- ሰዎች የራሳቸውን አድልዎ እንዲተቹ እና እንዲማሩ ማድረግ፣

## አባሪ

## የትምህርት እቅድ ሞዴል፤

❖ የመማር ችሎታ፡

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ።

- የባህል ብዝሃነትን ትርጉም ያብራራሉ፤

❖ **ይዘት፡** የባህል ብዝሃነትን ትርጉም

| ደቂ ቃ | የመምህራን እንቅስቃሴዎች | የተማሪ እንቅስቃሴዎች |
|---|---|---|
| 5’ | **መግቢያ**<br>- ያለፉትን ትምህርቶች በማስታወስ<br>- ዕለታዊ ትምህርቶችን ያስተዋውቁ<br>- የመማር ዓላማዎችን ይግለጹ<br>- አነቃቂ ጥያቄዎችን ይጠይቁ<br>- አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን ያደራጁ ምላሽ እና አስተያየት ለመስጠት፡፡ | - ያለፉትን ትምህርቶች ማስታወስ<br>- ከቀኑ ትምህርቶች ጋር መተዋወቅ<br>-ለትምህርታዊ ሥራዎች አስተዋፅዖ ያድርጉ፣<br>- በግል ይስሩ፣ ሀሳባቸውን ይፃፉ፣ እና ሀሳባቸውን ለሌሎች ተማሪዎች ያካፍሉ።<br>-አዕምሮን የሚያነቃቁ ጥያቄዎችን ይመልሱ፤ |
| 20’ | **የትምህርት ዝግጅት አቀራረብ**<br>• ፖስተር ወይም ምስል አሳይ፣<br>• የባህል ብዝሃነት ጽንሰ-ሀሳብን፣ ትርጉሙን እና የባህል ብዝሃነትን መሰረት ያብራሩ፡፡ | - ምስሎችን ይመልከቱ እና ያጥኑ።<br>- ማዳመጥ እና አጭር ማስታወሻ መውሰድ<br>- ጽሑፍ ያንብቡ፣ ያዳምጡ፣ ይረዱ፣ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፣ ጥያቄዎችን በመመለስ እና ሃሳባቸውን ለሌሎች ተማሪዎች በማካፈል ይሳተፉ። |
| 10’ | **ትምህርቱን አጠናክር**<br>-ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ተማሪዎችን ሀሳብ እንዲሰጡ ይፍቀዱ<br>ጥያቄያቸውን ለመመለስ፣<br>የተማሪዎችን ትምህርት እንዲማሩ ለማመቻቸት<br>ትምህርቱን ለማጠቃለል፡፡ | ለመወያየት፣ ለመተንተን እና በመጨረሻም የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ቡድኖችን ይፍጠሩ፤ የውይይታቸውን ነጸብራቅ ለክፍሉ ያቅርቡ። |
| 5’ | **ግምገማ**<br>የእለቱን ትምህርት ባጭሩ አሳጥረው | -የትምህርቱን ማጠቃለያ በጥንቃቄ ያዳምጡ።<br>- አጫጭር ጥያቄዎችን ይመልሱ፤<br>- ግልጽ ያልሆኑ ነጥቦችን ዝርዝሮችን ይጠይቁ። |

| | | |
|---|---|---|
| | ለተማሪዎች ያቅርቡ እና ጥያቄዎችን ይጠይቁ፤ ከዚያም ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት እንደገና እንዲያጠቃልሉ በማድረግ እና ምን ያህል እንደተረዱ ይገምግሙ። | - መልሶቹን ያዳምጡ |
| | **መርጃ መሳርያ፤**- የመማሪያ መጽሃፍቶች፣ ጥቁር ሰሌዳዎች እና ሌሎች ትምህርታዊ ቁሳቁሶች እንደ ስዕሎች እና ፎቶግራፎች ያሉትን መጠቀም፡፡ | |

የትምህርት ግምገማ

- ትክክል የሆነው ምንድን ነው? ______________________________________________
______________________________________________
- ምን ስህተት ተፈጠረ? ______________________________________________
______________________________________________
- በሚቀጥለው ጊዜ ለማሻሻል/ለመሞከር የሚፈልጉት ጠቃሚ ነገር ምንድን ነው? ______________________

# 3ኛ ክፍል ሲለበስ

# ምዕራፍ አንድ: ሰብአዊ ክበሬታ

……………(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:**

- የሰብአዊነት ትርጉም ይገልፃሉ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፤
- የሰብአዊ ክበሬታ አስፈላግነት ይለያሉ፤
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን በተግባር ያሳያሉ፤
- ሰዎች ካለመኖራቸዉ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ይለያሉ፡፡

| የመማር ብቃት | ይዘቶች | የመማር ዘዴዎች | ግምገም |
|---|---|---|---|
| • የሰብአዊነትን ትርጉም ይገልፃሉ፤<br>• የሰውን ልጅ ትርጉም ይገልፃሉ፤<br>• ለሰው ልጅ ክበሬታን ያሳያሉ፤ | 1.1 ሰብአዊነት<br>1.2. የሰው ልጅ ክበሬታ<br>1.2.1.የሰው ልጅ ክበሬታ አስፈላግነት<br>1.3.መሰረታዊ የሰው ልጅ ባህሪ<br>• ፍቅር<br>• የዋህነት<br>• መስጠት<br>• በጎ አድራጎት | ተማሪዎች ሁለት ሁለት በመሆን እንድወያዩ ማድረግ ሰብአዊነት ማለት ምን ማለት ነው?<br>• ተማሪዎችን በማሳተፍ እንድወያዩ ማድረግ፤ የሰው ልጅ ክበሬታ እና አስፈላግነት ላይ እንድወያዩ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች በሰው ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት ላይ | • ተማሪዎች ስለ ሰው ልጅ እንድገልፁ መጠየቅ፤<br>• የክፍል ውስጥ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በመመልከት ማግኘት የሚገባቸውን እዉቀት ማግኘታቸወርን ማረጋገጥ፤<br>• በተማሩት ላይ ጥያቄና መልስ ማካሄድ፤<br>• እያንዳንዱ ተማሪ ለተጠየቁት ነገር መልስና የሚፈለገው ሀሳብ ማስጠታቸውን መከታተል፤<br>• ፈተና መስጠት፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የሰው ልጅ ከበሬታን ያረጋግጣሉ፤<br>• መሰረታዊ ለሆኑ የሰው ልጅ ባህሪያት ዋጋ ይሰጣሉ፤<br>• መሰረታዊ የሰው ልጅ ባህሪያን ያሳያሉ፤<br>• ለሰው ከበሬታ አለመስጠት የሚመጡ ጉዳት ይገልፃሉ፤ | • ቸር መሆን<br>• ወንድማማችነት<br>• ታጋሽ መሆን<br>• ሰላም<br>• ማክበር<br>• ሀቀኝነት | ሚና በመጫወት እንድወያዩ ማመቻቸት፤<br>• መምህራን ሁኔታዊ ጥናት ማሰረት በማድረግ መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያትን ማስተማር ይቻላል፡፡<br>• አምስት አባላት ያለው ቡድን በማቀናጀት መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ባህሪያት ላይ በጥልቀት እንድወያዩ ማድረግ ነው፡፡<br>• ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎች ላይ ሁለተ ሁለት በመሆን እንድወያዩ ማድረግ ነው፡፡ | |

# ምዕራፍ 2: ሰዎችን ማክበር ..................(የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት 20)

## የምዕራፍ የመማር ውጤቶች

- ✓ ሰዎችን የማክበር ምንነት ይገልፃሉ፤
- ✓ ሌሎች ሰዎችን የማክበር  አስፈላግነት ይገልፃሉ፤
- ✓ ሌሎች ሰዎችን ሃሳብ እና ፍላጎት ያደንቃሉ፤
- ✓ ክብር ያላቸው ሰዎች ባህሪያትን ያሳያሉ፤ ¡
- ✓ ካለመከባበር ልመጡ የሚችሉ ችግሮችን ይለያሉ፡፡

| የመማር ብቃት | ይዘቶች | የመማር ዘዴዎች | ግምገም |
|---|---|---|---|
| • ሌሎች ሰዎችን ማክበር ጠቀሜታን ይገልፃሉ፤<br>•ሌሎች ሰዎችን የማክበር አስፈላግነት ዋጋ ይሰጣሉ፤<br>• የሌሎች ሰዎች አመለካከት እና ፍላጎት ያከብራሉ፤<br>• ከበሬታ ያላቸው ሰዎች ባህሪያትን ያሳያሉ፤ | 2.1. ሌሎች ሰዎችን ማክበር<br>2.2. ሌሎች ሰዎችን የማክበር አስፈላግነት<br>2.2.1. አረጋዊያንን ማክበር<br>2.2.2. የሃይማኖት አባቶችን ማክበር<br>2.2.3. መምህራንን ማክበር<br>2.2.4. ቤተሰብን ማክበር<br>2.2.5. ጎረቤትን ማክበር | • ሌሎች ሰዎችን ማክበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን እንድወያዩ ማድረግ፤<br>• ሌሎች ሰዎችን የማክበር አስፈላግነት ምን እንደሆነ ሁለት በሁለት እንድወያዩ ማድረግ፤<br>• መምህራን በይዘት 2.1. ስር የተዘረዘሩትን እንዴት እንደሚያከብሩ እንድጫወቱ ማድረግ ይቻላል፡ | • ተማሪዎች ሌሎች ሰዎች የማክበር ፅንሰ ሃሳብ እንድናገሩ መጠየቅ፤<br>• የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በመከታተል ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • .ሌሎች ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎችን ይገልፃሉ፡፡ | 2.2.6. የክፍል ጋደኞችን ማክበር<br>2.3. ከበሬታ ያላቸው ሰዎች ባህሪያት<br>2.4.ሌሎች ሰዎችን ካለማክበር የሚመጡ ተፅዕኖዎች | • አምስት አባላት ያለው ቡድን በማደራጀት የተከበረ ሰው ባህሪ ላይ እንድወያዩ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች የተከበረ ሰው ባህሪ ሚና በመጫወት እንድያሳዩ መርዳት፤<br>• የገለፃ ዘዴን በመጠቀም ሰዎችን ካለማክበር የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን ምሳሌ በመዉሰድ እንድወያዩ ማድረገወ ነው፡፡ | • በተማሩት ላይ ጥያቄና መልስ ማድረግ<br>• እያንዳንዱ ተማሪ የሚፈለገዉን ሃሳብ እና መልስ መስጠታቸዉን መከታተል፤<br>• የቤት ሥራን መስጠት፡፡ |

# ምዕራፍ 3 እኩልነት

## የተመደበለት ክ/ጊዜ 20

## የመማር ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የእኩልነትን ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፤
- በትምህርትቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚገኘው የእኩልነት መብት ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ፤
- በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ መካከል የእኩልነትን አመለካከት ያሳያሉ፤
- በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚፈጠርን የአድሎ ተፅዕኖ ይለያሉ ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማርማስተማርዘዴዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የእኩልነትን ምንነትይገልፃሉ፡፡ በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚገኘው የእኩልነት መብት ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ፡፡ | 3.1 እኩልነት<br>3.2 የእኩልነት መብት በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ<br>3.2.1 የስርዐተ ፆታ እኩልነት<br>3.2.2 የቋንቋ እኩልነት<br>3.2.3 የሐይማኖት እኩልነት | • የእኩልነት ፅንሰ ሀሳብ ላይ ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩ ማድረግ<br>• በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚያስፈልግ እኩልነት ተማሪዎቹን በቡድን በመከፈል እንዲወያዩ አድርጉ፡፡ | ተማሪዎች የእኩልነትን ፅንሰ ሀሳብ እንዲገልፁ ይጠይቁ<br>ተማሪዎች በሚሳተፉበት ወቅት በማየት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| በትምህርት ቤትና በህብረተሰቡ መካከል እኩልነት ይስተናገድበት የነበረበትን ልምድ ያሳያሉ፡፡<br><br>የእኩልነት አለመኖር ጉዳቶችን ይለያሉ፡፡ | 3.2.4የባህል እኩልነት<br><br>1. የእኩልነት አስፈላጊነት<br><br>የእኩልነት አለመኖር የሚያስከትላቸው ጉዳቶች | • በእኩልነት አለመኖር ሊመጣ ስለሚችለው ጉዳት ተማሪዎች በብድን በመሆን ይወያዩ፡፡<br>• ተማሪዎችን በሁኔታዎች ጥናት ላይ ያሳትፉ | መመዝገብ<br><br>የተማሪዎችን መማር ለማሻሻል በገለፃ የተደገፈ ግብረ መልስ ይስጡ |

# ምዕራፍ 4 ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት

## የተመደበለት ክፍል ጊዜ 18

## የመማር ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የጤናማ ማህበራዊ ሕይወትን ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፤
- የጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያትን ይገልፃሉ፤
- የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፤
- ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን ያሳያሉ፤
- ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን የሚጎዱ ነገሮችን ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማርማስተማርዘዴዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የጤናማ ማህበራዊ ሕይወትን ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ<br><br>የጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያትን ይለያሉ | የጤናማ ማህበራዊ ሕይወትን ፅንሰ ሀሳብ<br><br>የጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያት | • ስለ ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ፅንሰ ሀሳብ በበድን በመሆን እንዲወያዩ ማድረግ<br>• አራት አባለት ያሉት ቡድን በመመስረት የጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ባህሪያትን በተለመከተ<br>• እንዲወያዩ ማድረግ | ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎችን መጠየቅ<br><br>የተማሪዎችን ተሳትፎ በመዘዋወር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፤<br><br>እርስ በርሳቸው መልካም ግንኙነት ያሳያሉ<br><br>በመልካም ማህበራዊ ሕይወት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ነገሮችን ይዘረዘራሉ | የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነት<br><br>መልካም ማህበራዊ ሕይወት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ነገሮች | • ተማሪዎችን በማሳተፍ የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈለጊነት ላይ የፒራሚድ ዘዴን በመጠቀም ማወያየት<br>• ተማሪዎች በጥንድ በመሆን በመልከም ማህበራዊ ሕይወት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነገሮች እንዲወያዩ ማድረግ | መመልከትና ከመማር ውጤትና ከሚጠበቀው የመማር ብቃት ጋር ተስማምቶ መሄዱን ማረጋገጥ<br><br>በተማሩት ትምህርት ላይ በመመርኮዝ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br><br>ተማሪዎች እያንዳንዳቸው ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ |

## ምዕራፍ 5፡ትብብር እና የቡድን ስራ

.............................................. ..........(የተመደበው ክፍል ጊዜ፡ 21)

የመማሪያውጤቶች፡በዚህምዕራፍመጨረሻላይተማሪዎችየሚከተሉትንማድረግይችላሉ።

» መረዳዳትእናየቡድንስራምንማለትእንደሆነያብራራሉ።
» በማኅበረሰባቸውእናበትምህርትቤቱውስጥየትብብርእናየቡድንስራባህልን ይለያሉ።
» የጨዋታእናየቡድንስራመርሆዎችንዋጋይሰጣሉ።
» የመረዳዳትእናየቡድንስራችሎታዎችንያሳያሉ።
» የመረዳዳትእናየቡድንስራንአስፈላጊነትያብራራሉ።

| የሚጠበቀው ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶች | ዳሰሳ/ክትትል |
|---|---|---|---|
| • የመረዳዳት እና የቡድን ስራ ትርጉም ሁኔታ መግለጽ፤<br>•ለህብረተሰባቸውን የመረዳዳት እና የቡድን ስራ ባህል ዋጋ ይስጡ ።<br>• የት/ቤታቸውንና የማህበረሰባቸውን የመረዳዳት እና የቡድን ሥራ መመሪያዎች | 5.1. መረዳዳት እና የቡድን ስራ<br>5.2. የመረዳዳት እና የቡድን ሥራ ባህል በማህበረሰብ እና በትምህርት ቤት ውስጥ<br>5.2.1. በማህበረሰብ ውስጥ<br>ሀ) ደቦ (ጂጊ)<br>ለ) እድር<br>5.2.2. በትምህርት ቤት ውስጥ<br>ሀ) የቡድን ስራ<br>5.3. የመረዳዳት እና የቡድን ስራ እሴቶች | • በክብ መልክ ቡድኖችን በማቋቋም የመረዳዳት እና የቡድን ሥራ ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩበት፡፡ ተማሪዎችን በማሳተፍ በማኅበረሰባቸው እና በትምህርት ቤት ውስጥ የመረዳዳት እና የቡድን ሥራ ባህል ላይ ይወያዩ፡፡ ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድኖች | • ተማሪዎች መረዳዳትን እና የቡድን ስራን ምን እንደሆኑ እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፤<br>• የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በክፍል ውስጥ መመልከት ከሚጠበቁ የትምህርት ውጤቶች እና ክህሎቶች ጋር መያያዙን ያረጋግጡ።<br>• ተማሪዎችን ስለተማሩት ትምህርት ይጠይቁ።<br>• እያንዳንዱ ተማሪ ምላሽ እንዲሰጥ ይሞክሩ፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መለየት፡፡<br>• የመረዳዳት እና የቡድን ስራ ችሎታዎች ማሳየት<br>• በመረዳዳት እና በቡድን ስራ አስፈላጊነት ላይ መወያየት፡፡ | 5.4. የመረዳዳት እና የቡድን ስራ ችሎታዎች<br>5.4.1. የአስተሳሰብ ግብረ መልስ ወይም ሀሳብ ለመቀበል እና ለመስጠት በአእምሮ መዘጋጀት<br>5.4.2. ተግባቦት<br>5.4.3. ድርጅት/ተቋም<br>5.4.4. ክርክር<br>5.4.5. የጊዜ አጠቃቀም<br>መንገዱን እየመራ<br>5.5.5. የመረዳዳት እና የቡድን ሥራ አስፈላጊነት | በመከፋፈል በመረዳዳት እና በቡድን ስራ መመሪያዎች ላይ እንዲወያዩ አድርጉ።<br>• ተማሪዎችን በማሳተፍ በተግባራዊ ለውጥ ዘዴዎች የመረዳዳት እና የቡድን ስራ ችሎታዎች ላይ ተወያዩ።<br>ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ያለውን መረዳዳት እና የቡድን ስራ በማስመሰል እንዲለማመዱ አድርጉ። | እያንዳንዱ ተማሪ መልስ እንዲሰጥ ይሞክሩ፤<br>ጥያቄዎች መጠየቅና ተገቢውን መልስ እና አስተያየትመስጠታቸውን መከታተል፤<br>የክፍል ሙከራ ይስጡ፤ |

## ምዕራፍ 6፡መድብለ-ባህላዊነት

.............................................. ..........(የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 20)

የመማሪያውጤቶች፡በዚህምዕራፍመጨረሻላይተማሪዎችየሚከተሉትንማድረግይችላሉ።

- የባህላዊልዩነትንትርጉምግለጽ።
- የባህልልዩነቶችንማስተናገድያለውንጠቀሜታአስረዳ።
- የማህበረሰባቸውንባህላዊልዩነትማድነቅ።
- የተለመደውንየተለያዩ ባህልባህሪያትንየማስተናገድ ሥራን ያሳያሉ።

| የሚጠበቀው ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶች | ዳሰሳ/ክትትል |
|---|---|---|---|
| • የማህበረሰባቸውን የባህል ብዝሃነትን ያብራራሉ።<br>• የማህበረሰቡን የባህል ብዝሃነት አይነት ይለያሉ፤<br>• የባህል ብዝሃነት ማስተናገድ አስፈላጊነት ዋጋ መስጠት፤<br>• የባህል ብዝሃነት ማስተናገጃ መንገዶችን ላይ መገለጫ ይሰጣሉ፤ | 6.1. የባህል ብዝሃነት ትርጉም<br>6.2. የማህበረሰብ የባህል ብዝሃነት አይነቶች<br>6.2.1.ጎሳ<br>6.2.2.የባህላዊ አልባሳት<br>6.2.3. ባህላዊ ዘፈን<br>6.2.4.የባህላዊ ምግብ<br>6.2.5.የባህላዊ ሠርግ<br>6.3. የባህል ብዝሃነት የማስተናገድ አስፈላጊነት። | • ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው በባህል ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ ላይ እንዲወያዩ ይጠይቋቸው።<br>• አምስት ተማሪዎችን አባላት ያቀፈ ቡድን በመመስረት በማኅበረሰባቸው የባህል ብዝሃነት ዓይነቶች ላይ እንዲወያዩ አድርጉ። | • ስለ የባህል ብዝሃነት ተማሪዎች እንዲናገሩ ይጠይቁ፤<br>• የሚጠበቁ ውጤቶች እና ክህሎቶች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ የተማሪ እንቅስቃሴዎችን በክፍል ውስጥ ይመልከቱ።<br>• በተማሩት ትምህርት ላይ ጥያቄ አቅርብ፤<br>• እያንዳንዱ ተማሪ ምላሽ ይሰጣል፣ ይሞክሩ እያንዳንዱ ተማሪ መልስ እንዲሰጥ ይሞክሩ፤ ጥያቄዎች መጠየቅና ተገቢውን መልስ እና አስተያየትመስጠታቸውን መከታተል፤<br>የክፍል ሙከራ ይስጡ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የማህበረሰባቸውን የባህል ብዝሃነት ያደንቃሉ። • የተለመደውን የባህል ብዝሃነት የማስተናገድ ባህሪን ያሳያሉ፤ | 6.4. የባህል ብዝሃነት ማስተናገጃ መንገዶች | • ስለ ብዝሃነት አስፈላጊነት መግለጫ በመስጠት መንገድ እንዲወያዩ ያድርጉ። • ተማሪዎች የማህበረሰባቸውን ልዩነት ማስተናገድ የሚችሉባቸውን መንገዶች በቡድን እንዲወያዩ ጠይቋቸው። | |